# መጽሐፈ ኢያሱ

ትምህርት አራት

## በቃል ኪዳን መታመን

ተርጓሚ፡ እሸቴ በለጠ

THIRD MILLENNIUM MINISTRIES

Biblical Education. For the World. For Free.

© 2017 by Third Millennium Ministries

All rights reserved. No part of this publication may be reproduced in any form or by any means for profit, except in brief quotations for the purposes of review, comment, or scholarship, without written permission from the publisher, Third Millennium Ministries, Inc., 316 Live Oaks Blvd, Casselberry, Florida 32707.

# እናስተዋውቅዎ

የሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ1997 ዓ.ም. ተመሠረተ፡፡ ይህ አገልግሎት አትራፊ ያልሆነ ድርጅት ሲሆን፣ **መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎችን ለመላው ዓለም በነጻ ለማዳረስ** የተቋቋመ ነው፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለውን ጤናማ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ - መሠረት ያለው ክርስቲያናዊ የአመራር ስልጠና ፍላጎት ምላሽ ለመስጠት፣ ምንም ዓይነት የስልጠና ግብዓቶች የማግኘት እድል ለሌላቸው ክርስቲያን መሪዎች የሴሚነሪ ሥርዓተ-ትምህርቶችን በማዘጋጀት እናሰራጫለን፡፡ ሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ በመላውም ዓለም ለሚገኙ ክርስቲያን መሪዎችና ፓስተሮች የተመጣጠነ ዋጋ ያለው፣ በደጋፊዎች የሚታገዝ፣ ለተጠቃሚው ምቹ፣ በልዩ ልዩ የመገናኛ ብዙሃን ዘዴዎች የታገዘ ሥርዓተ-ትምህርት በአምስት ቋንቋዎች (በእንግሊዝኛ፣ በስፓኝ፣ በራሺያኛ፣ በማንዳሪን ቻይንኛ እና በአረብኛ) አስተርጎሞ አሰራጭቷል፡፡ ሁሉም ትምህርቶች የተጻፉት፣ የተዘጋጁት እና የታተሙት በአገልግሎቱ ውስጥ ሲሆን በ The History Channel©. ካሉት ጋር በቅርፅና በጥራት ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ የሰርድ ሚሊኒየም ሥራ ማለትም ጥራት ላለው የማስተማሪያና የአኒሜሽን የቪዲዮ ፕሮዳክሽን ሥራዎቹ ሁለት የቴሊ አዋርድ ሽልማቶችን ተቀብሏል፡፡ የማስተማሪያ ግብዓቶቻችን በዲቪዲ፣ በህትመት፣ በኢንተርኔት ማስተላለፊያ ዘዴዎች፣ በሳተላይት የቴሌቪዥን ስርጭት፣ በራዲዮና በቴሌቪዥን ስርጭቶች ለማቅረብ በሚያስችል መልክ የተቀረፁ ናቸው፡፡ ሥርዓተ-ትምህርታችን በአሁኑ ወቅት ከ192 በላይ በሆኑ አገሮች ውስጥ አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡

ስለ አገልግሎታችን የበለጠ መረጃ ለማግኘትና እንዴት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆን እንደምትችሉ ማወቅ ከፈለጋችሁ፣ www.thirdmill.org የተሰኘውን ድረ-ገጽ ጎብኙ፡፡

**ማውጫ**


1. **መግቢያ**
2. **የቃል ኪዳን ማስጠንቀቂያዎች**

   **ሀ. አወቃቀርና ይዘት**

   1. የኢያሱ ስብሰባ
   2. የኢያሱ ንግግር

      2.1 ኢያሱ 23፡2-8

      2.2. ኢያሱ 23፡9-13

      2.3. ኢያሱ 23፡14-16

   **ለ. ቀደምት ትርጓሜ**

   1. መለኮታዊ ሥልጣን
   2. የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን
   3. የሙሴ ህግ ስነ-ልክ
   4. የእግዚአብሔር ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይል
   5. እስራኤል በጠቅላላ

3. **የቃል ኪዳን መታደስ**

   **ሀ. አወቃቀርና ይዘት**

   1. ስብሰባዎች
   2. ንግግርና ምላሾቹ

      2.1. የመጀመሪያ ጥሪና ምላሹ

      2.2. ሁለተኛ ጥሪና ምላሹ

      2.3. ሦስተኛ ጥሪና ምላሹ

   3. ህግን የማጽደቅ በዓል
   4. ወደየርስት መመለስ

   **ለ. ቀደምት ትርጓሜ**

   1. መለኮታዊ ሥልጣን
   2. የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን
   3. የሙሴ ህግ ስነ-ልክ
   4. የእግዚአብሔር ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይል
   5. አስራኤል በጠቅላላ

4. **ክርስቲያናዊ ተዛምዶ**

   ሀ. ብሥራት

   ለ. መስፋፋት/እድገት

   ሐ. ፍጻሜ

5. **ማጠቃለያ**

# መግቢያ

አንድ ተዋናይ በሁሉም ትዕይንት ውስጥ የመሪነትን ስፍራ የሚይዝበትን አንድ ቲያትር እየተመለከታችሁ እንደሆነ አድርጋችሁ አስቡ፡፡ እርሱ የሚያደርገው ነገር ባሪኩ ውስጥ እጅግ ወሳኝ ነገር እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ ሆኖም በመጨረሻው ትዕይንት ላይ፣ ወደ መድረኩ ማዕከላዊ ክፍል ወጣ ይልና የአጠቃላይ ድራማው ወሳኝ አካላት ተደራሲያኑ መሆናቸውን ያብራራል፡፡

እንግዲህ፣ በበርካታ መንገዶች፣ በኢያሱ መጽሐፍ ውስጥ የሆነው ነገር ይኸው ነው፡፡ በመጽሐፉ ውስጥ ከዳር እስከዳር የመሪነቱን ሚና የሚጫወተው ኢያሱ ነበር፡፡ እርሱ የሚያደርጋቸው ነገሮች ሁሉ እጅግ ወሳኞች ናቸው፡፡ ግን በመጨረሻዎቹ ትዕይንቶች ውስጥ፣ ሁለት ንግግሮችን አድርጓል እነዚያንም ጸሐፊው በመጥቀስ የጠቅላላ መጽሐፉ ዋና ጉዳይ እስራኤልን ህዝብ የሚመለከት ጉዳይ እንደሆነ ለማመልከት ተጠቅሞበታል፡፡

መጽሐፈ ኢያሱ ከተሰኘው ተከታታይ ትምህርታችን ይህኛው አራተኛው ትምህርት ሲሆን፣ የእስራኤል “በቃል ኪዳን መታመን” የሚል ርዕስ ሰጥተነዋል፡፡ በዚህ ትምህርት፣ የኢያሱ መጽሐፍ ሦስተኛውና የመጨረሻው ክፍል የመጽሐፉን ወሳኝነት ይገልጽልናል፡፡ ይህንንም የሚያደርገው ከእግዚአብሔር ጋር ለገቡት ቃል ኪዳን ታማኝ ሆነው እንዲዘልቁ ለእስራኤላውያን ጥሪውን ለማቅረብ ነው፡፡

በዚህ ተከታታይ ትምህርት ጅማሬ ላይ፣ የኢያሱ መጽሐፍ ቀደምት ትርጉም እንዲህ ጠቅለል ብሎ ሊቀርብ እንደሚችል ገልጸን ነበር፡፡

> ***የኢያሱ መጽሐፍ የተጻፈው በኢያሱ ዘመን የተከናወነውንና መጪው ትውልድ በዘመኑ ሊገጥመው የሚችለውን ተመሳሳይ ፈተና እንዲቋቋም በሚያስችለው መንገድ የእስራኤልን በድል አድራጊነት መውረስ፣ የነገዶችን ርስት ክፍፍል እና በቃል ኪዳን መታመን ለማሳየት ነው፡፡***

መጽሐፉ በተቀዳሚነት የተቀናበረው በመሳፍንት ዘመን፣ በነገሥታት ዘመን፣ ወይም ወደ ኋላ ላይ በባቢሎን ምርኮ ዘመን የኖሩትን የብሉይ ኪዳን እስራኤላውያን ለመምራት ነው፡፡ የሚዳስሰውም ቀደምት ተደራሲያኑ ጠላቶቻቸውን እንዴት ሊጋፈጡ እንደሚገባ፣ የገዛ ምድራቸውን እንዴት መያዝ እንዳላባቸው እና እንደ እግዚአብሔር የቃል ኪዳን ሕዝብ ያሉዋቸውን በረከቶችና ሃላፊነቶች ነው፡፡

ቀደም ባሉት ትምህርቶች እንደተማርነው፣  ወደዚህ ግብ ለመድረስ፣ ጸሐፊአችን መጽሐፉን በሦስት ዋና ክፍሎች ከፋፍሎታል፡፡ ከምዕራፍ 1-12፣ በእስራኤል በድል አድራጊነት መውረስ ላይ አተኩሯል፡፡ ከምዕራፍ 13-22፣ ትኩረቱን በእስራኤል ነገዶች የርስት ክፍፍል ላይ አድርጓል፡፡ በምዕራፍ 23 እና 24 ውስጥ፣ እስራኤል ሊኖራት በሚገባው የቃል ኪዳን መታመን ላይ ትኩረት አድርጓል፡፡ በዚህ ትምህርት፣ ይህንን ዋና ክፍል እንመከታለን፡፡

የኢያሱ መጽሐፍ ሦስተኛ ክፍል ሁለት ዋና ክፍሎችን እና ማጠቃለያን ያካትታል፡፡ የሚጀምረው በ 23፡1-16 ውስጥ በሚገኘው ንግግር ሲሆን፣ በዚያም ኢያሱ ለእስራኤል የቅል ኪዳን ማስጠንቀቂያ ሰጥቶበታል፡፡ ከዚያም በ 24፡1-28 ወደሚገኘው ሁለተኛ ንግግር ይሸጋገራል በዚያም የቃል ኪዳን ተሃድሶ ክብረ በዓልን የጠቀሰ ሲሆን ከቁጥር 29-33 የሚገኘውናና የኢያሱን ሞትና በተከታታይ የተከናወኑ ክንውኖችን የዘገበውን ማጠቃለያ ስከትላል፡፡

በእስራኤል የቃል ኪዳን መታመን ላይ የሚያተኩረው ትምህርታችን እነዚህን የማጠቃለያ ምዕራፎች በሦስት እርከኖች ይከፍላቸዋል፡፡ አስቀድመንም ኢያሱ በመጀመሪያው ንግግሩ ስለሰጠው የቃል ኪዳን ማስጠንቀቂያ ከዚያ ደግሞ ስለ ቃል ኪዳን ተሃድሶ በመጨረሻም ተከትሎ ስለሚመጣው የማጠቃለያ ሃሳብ ጥቂት ሃሳቦችን እንሰነዝራለን፡፡ በመጨረሻም፣ የመጽሐፋችንን የዚህን  ክፍል ክርስቲያናዊ ተዛምዶ እንመረምራለን፡፡ አስቀድመን ኢያሱ በሰጠው የቃል ኪዳን ማስጠንቀቂያ እንጀምር፡፡

# የቃል ኪዳን ማስጠንቀቂያዎች

መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውቀት ያለው ማንኛውም ሰው እንደሚረዳው ተደራሲያኖቻቸው በእግዚአብሔር ላይ እንዳያምፁ የብሉይ ኪዳንም ሆነ የአዲስ ኪዳን ጸሐፍት ደጋግመው ያሳስቡ ነበር፡፡ ሆኖም ግን በርካታ ወንጌል አማኞች እነዚህን ማስጠንቀቂያዎች ከመጽሐፍ ቅዱሳዊው "የቃል ኪዳን" ሃሳብ ጋር ለማገናኘት ዝግጁ አይደሉም፡፡ ይልቁኑ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ከበረከቶቹ ጋር ብቻ ወደ ማያያዝ እናዘነብላለን፡፡ እንግዲህ፣ በእነዚህ ተከታታይ ትምህርቶች እንደተመለከትነው እግዚአብሔር በቃል ኪዳኑ አማካይነት በጎነቱን ለእስራኤል እንዴት እንደገለጸ የኢያሱ መጽሐፍ ጸሐፊ ትኩረታቸውን እንደሳበ ተመልክተናል፡፡ ሆኖም ጠጋ ብለን ስንመለከተው፣ የእግዚአብሔር ህዝብ የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ሲተላለፉ ስለሚያመጣው ፍርድ የሚሰጠውን ማስጠንቀቂያ በመጽሐፋችን በምእራፍ 23 ላይ ተጽፎ እናስተውላለን፡፡

ኢያሱ የሰጠውን የቃል ኪዳን ማስጠንቀቂያ በተለመደው ንድፍ መሰረት ወደ መመልከቱ እንሸጋገራለን፡፡ በመጀመሪያ፣ የዚህን ክፍል አወቃቀርና ይዘት እንመለከታለን፡፡ ሁለተኛ ደግሞ፣ በቀደምት ትርጓሜው ላይ እንነጋገራለን ወይም ተቀዳሚ ተደራሲያኑ ላይ በጎ ተፅዕኖ ለማሳደር እንዴት እንደተነደፈ እንመለከታለን፡፡ የዚህን ምዕራፍ አወቃቀርና ይዘት በመመልከት እንጀምር፡፡

## አወቃቀርና ይዘት

ኢያሱ እስራኤላውያንን ወደ ከነዓን እምብርት በድል እንደመራቸው፣ ደግሞም በሰሜንና በደቡብ ዋና ዋና ዘመቻዎችን እንዳካሄደም ታስታውሳላችሁ፡፡ ለየነገዶቻቸው ወደተመደበላቸውና ከዮርዳስ ማዶና ከዮርዳኖስ ወዲህ ወዳሉ ርስቶቻቸው እንዲሄዱና እንዲሰፍሩ ሲያደርግም የእስራኤልን አንድነት እንዴት እንዲጠበቅ እንዳደረገም እናስተውላለን፡፡ ሆኖም በመጽሐፉ በዚህኛው ነጥብ ላይ፣ ጸሐፊአችን፣ ኢያሱ በጠራው ስብሰባ ምናልባትም በሴሎ፣ ያም በኤፍሬም ድንበር ላይ በተካሄደው ስብሰባ ላይ ያተኩራል፡፡ እስራኤል በዚያ ስፍራ ከኢያሱ ወሳኝ መመሪዎችን ለመስማት ተሰብስበው ነበር፡፡

ለእኛ ዓላማ ግን፣ ይህንን ምዕራፍ በሁለት እርከኖች ከፍለን መመልከት ይጠቅማል፣ በምዕራፍ 23፡1-2ሀ ላይ በሚጀምረው ማሳሰቢያ እንጀምር፡፡

### የኢያሱ ማሳሰቢያዎች (የክስ መጥሪያ ዓይነት)

በርካታ ጊዜያት ኢያሱ እስራኤልን የሰበሰበባቸውን ወቅቶች የኢያሱ መጽሐፍ እንደሚጠቃቅስ ማስታወስ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ ሆኖም የዚህኛው ማሳሳቢያ መግለጫ እንደሚያመለክተን ኢያሱ እስከ አሁን ካደረጋቸው ስብሰባዎች ይልቅ ይህኛው የላቀ ፋይዳ እንዳለው ጸሐፊአችን ያመለክተናል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ፣ በ 23፡1 ላይ፣ ኢያሱ እንዳረጀና እድሜው እንደገፋ ጸሐፊአችን ይጠቅስልናል፡፡ ይኸው ተመሳሳይ መግለጫ በመጽሐፉ ሁለተኛ ክፍል መጀመሪያ በ13፡1 ላይም የተጠቀሰ ሲሆን፣ በዚህ ስፍራ ግን "ብዙ ዘመን አለፈ" የሚል ተጨማሪ ማስታወሻ ተጠቅሶ እናገኛለን፡፡ በዚህኛው ተመሳሳይ ስፍራ በ23፡2 ላይ፣ ኢያሱ ንግግሩን የሚጀምረው "እኔ አርጅቻለሁ ዕድሜዬም ገፍቷል" በማለት ነው፡፡ ደግሞም በቁጥር 14 ውስጥ፣ "እነሆ አሁን የምድሩን ሁሉ መንገደ ልሄድ ነው" የሚል ሃሳብም ያክልበታል፡፡ ጸሐፊአችንም የኢያሱ በእድሜ መግፋት ጉዳይ ይህኛው ስብሰባ ለኢያሱ እንደ እስራኤል መሪ ከሚያከናውናቸው ወሳኝ ተግባራት መካከል አንዱና ወሳኙ እንደሆነ አጽንዖት ያደርግበታል፡፡ በዚህም ዘመን ሰዎች በሞት አፋፍ ላይ ያለን ሰው የመጨረሻ ንግግሮች ትኩረት እንደሚያደርጉባቸው ሁሉ፣ ቀደምት ተደራሲያኑ የሆኑት የታመኑ እስራኤላውያንም ይህ ወቅት እጅግ ወሳኝ ወቅት እንደሆነ ይገነዘባሉ፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ፣ 23፡2 እንደሚያስቀምጠው፣ "ኢያሱ እስራኤልን ሁሉ አለቆቻቸውን፣ መሪዎቻቸውን፣ ፈራጆቻቸውንና ሹማምቶቻቸውን ሁሉ ጠርቶ እንዲህ አላቸው" ይላል፡፡ ኢያሱ በዚህ ስፍራ እያናገረ ያለው ሊቀ ካህኑን ወይም ከፍተኛ እርከን ላይ ያሉትንና ከመደበኛውና ከአብዛኛው የእስራኤል ህዝብ ለየት ብለው የሚኖሩትን ሌዋውያንን አልነበረም፡፡ ይልቁኑ፣ ያናገረው ከህዝቡ ጋርደጋግመው በሚገናኙ በተለያየ ደረጃ ላይ በሚገኙ መሪዎች አማካይነት "መላውን እስራኤልን" ነበር፡፡ ኢያሱ የተናገረውን ነገር የማጽናቱና የማጠናከሩ ሃላፊነት "የሽማግሌዎች፣ የአለቆች ...

የመሳፍንትና የመኮንኖች” ነው፡፡ ስለዚህ፣ በዚህ ጉባኤ ላይ የምናስተውለው፣ ኢያሱ እያነሳ ያለው ጉዳይ መላውን እስራኤልን የሚነካና ከዕለት ከዕለት ሕይወቱ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ጉዳዮች ነው፡፡

ግን ስለዚህ ጉባኤ ዋናው ጉዳይ ምንድን ነው? ለዚህ ነገር ምላሽ የሚገኘው በሁለተኛው እርከን በምዕራፍ 23 ውስጥ በሚገኘው የኢያሱ ንግግር ውስጥ ነው፡፡ ከቁጥር 2ለ-16 ውስጥ፣ እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን እንዳይተላለፉ ኢያሱ ያስጠነቅቃል፡፡

## የኢያሱ ንግግር

ስለ መለኮታዊ ቃል ኪዳናት በበለጠ ጥልቀት ከዚህ ቀደም ተመልክተናል፡፡ በአጭሩ ለማስቀመጥ ግን፣ መለኮታዊ ቃል ኪዳናት እግዚአብሔር በመንግሥቱ ውስጥ የደነገጋቸውን ማዕከላዊ የአስተዳደር ፖሊሲዎች የሚገልጡ ናቸው፡፡ የእነዚህን መለኮታዊ ቃል ኪዳነን ፖሊሲዎች ልዩ ልዩ ገጽታ በሦስት ዋና ዋና ጎራዎች መክፈል እንችላለን፡ መለኮታዊ በጎነት፣ ሰብዓዊ ታማኝነት፣ ተከትለው የሚመጡ በረከትና መርገሞች፡፡

ስለ መለኮታዊ በጎነት በምንናገርበት ወቅት በልቡናችን የያዝነው የእግዚአብሔር በጎነት የቃል ኪዳናቱ ሁሉ ምንጭና ቃል ኪዳናቱንም እስከፍፃሜ የሚያጸናው እንደሆነ ማሳየትን ነው፡፡  ሰዎች መቼውንም ቢሆን ከእግዚአብሔር ጋር የሚደረጉ ቃል ኪዳናት ጠንሳሽ ሊሆኑና በራሳቸው አቅምና ችሎታ ሊያስቀጥሉ አይችሉም፡፡ ሁልጊዜ መለኮታዊ በጎነት ወሳኝነት አለው፡፡ በተመሳሳይ መንገድ ግን፣ እግዚአብሔር በቃል ኪዳኑ አማካይነት የሚገልጠው በጎነት ሰዎች በአክብሮት ታማኝነታቸውን እንዲያሳዩ ይጠብቅባቸዋል፡፡ ሰዎች እግዚብሔር ካደረገላቸው ነገር የተነሳ ለእግዚአብሔር የታመነ አገልግሎታቸውን እንዲያቀርቡ በተደጋጋሚ ታዝዘዋል፡፡ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተገለጠው ደግሞ፣ የእግዚአብሔር ቃል ኪዳናት ዘወትር በረከትን ወይም ምግምን አስከትለው እንደሚመጡ እንገነዘባለን፡፡ የእግዚአብሔር ህዝብ ለእርሱ ታማኝ ሲሆኑና ህግጋቱን ሲጠብቁ፣ የእርሱን የተትረፈረፉ በረከቶች ይቀበላሉ፡፡ ከታማኝት ሲጎድሉና ትዕዛዛቱን ሲተላለፉ ግን፣ የእርሱ እርግማን ይደርስባቸዋል፡፡

የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች ደጋግመው እንዳመለከቱን እነዚህ የቃል ኪዳን ገጽታዎች በተለያዩ ዘመናት ምሥጢራዊ በሆኑ መንገዶች እንደተገለጡ ያመለክቱናል፡፡ የእግዚአብሔር ትዕግሥትና ይቅርታ፣ ደግሞም የእርሱ ቁጣና ፍርድ፣ በተገለጡ ቁጥር ዘወትር እንደነቃለን ምክንያም እርሱ መንገዶች ከእኛ አቅምና መረዳት እጅግ ስለሚልቁ ነው፡፡ የመጽሐፍቀ ቅዱስ ጸሐፊዎች ግን እግዚአብሔር ዘወትር ለቃል ኪዳኖቹ ታማኝ እንደሆነ ደግሞም ሊነገር በማይችለው መልካምነቱ፣ እውቀቱና ጥበቡ እንደሚመራቸው  ደግመው ደጋግመው ማረጋገጫ ይሰጡናል፡፡

ከእነዚህ ከሦስቱ የቃል ኪዳን ገጽታዎች ጋር በቀጥታ ሚገናኘውን በምዕራፍ 23 የሚገናኘውን የኢያሱን ንግግር ለመመልከት ተዘጋጅተናል፡፡ አስቀድመን ግን፣ እስራኤል ለእግዚአብሔር እያሳዩ ያሉት ከታማኝነት የመጉደል አደጋና ተከትሎ ስለሚመጣውም መርገም ኢያሱ ማስጠንቀቂያ መስጠቱን ማሳሰብ እንወዳለን፡፡

> *በምዕራፍ 23 ውስጥ ኢያሱ ህዝቡን ሲያናግር፣ በመጀመሪያዎቹ 16 ቁጥሮች ውስጥ፣ ስለ ቃል ኪዳኑ ማስጠንቀቂያዎች ተናግሯል፡፡ ለቃል ኪዳኑ  ታማኝ ሆነው መዝለቅ እንደሚገባቸው መታዘዛቸውን ያሳስባቸዋል፡፡ መጽሐፉ በጠቅላላ የሚያወሳው ስለ ቃል ኪዳኑ አምላክ ስለ እግዚአብሔር፣ ስለዚህ አምላክ በጎነት፣ ውጊያቸውን ስለሚዋጋላቸው አምላክ፣ ድልንም ስለሚሰጣቸው አምላክ፣ ጥቃውንም በልጆቹ ላይ ስለሚያጸናው አምላክ፣ ምገሱን ስለሚያፈስሰው አምላክ፣ ከሁሉ በላይ ግን፣ እኛ በታማኝነት እንድንዘልቅ የሚጠብቅ አምላክ ስለ መሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ፣ ኢያሱ ለህዝቡ ስለመታዘዝና መታዘዝን ተከትለው ስለሚመጡ በረከቶች ደግሞም ስላለመታዘዝና አለመታዘዝን ተከትለው ስለሚመጡ እርግማኖች ይነግራቸዋል፡፡ ልክ እንደ ሌሎቹ ቃልኪዳኖች ሁሉ ይህኛውም፣ የያዘው ነገር አለ ያም፣ እንድ ብርቱ ንጉሥ ከደካማ ንጉሥ ጋር እንደሚገባው ቃል ኪዳን ዓይነት ሳይሆን ደግሞም አንደ ብርቱ ንጉሥ ስለ ገባው የበጎነት ቃል ኪዳን ብቻ የሚያወሳ ሳይሆን እኛም ለቃል ኪዳኑ ታማኝ ሆነን መዝለቅ እንደሚገባንና የመታዘዝንና ያለታዘዝን ብድራቶች፣ የመታመንንና ያለመታመንን ብድራቶችም ያካተተ ቃል ኪዳን ነው፡፡ በጠቅላላ መጽሐፉ ውስጥ ስለ እግዚአብሔር ታላቅነት፣ ሁሉን ማድረግ ስለሚችለውና ስላደረገው ስለ ቃል ኪዳኑ አምላክ፣ ያም የሆነው ስለሚገባን ሳይሆን እርሱ ከእኛ ጋር ቃል ኪዳን ሊያደርግ*

*ስለወደደደ እንደሆነ ከጠቀሰ በኋላ ኢያሱ፣ ህዝቡ ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆነው መዝለቅን እንዳይረሱ በብርቱ ያሳስባቸዋል፡፡*

*ፓስተር ኦርናን ክሩዝ፣ ተተርጉሞ የቀረበ*

ምንም እንኳን ይህንን በመሰለ ወሳኝ ስብሰባ ላይ ኢያሱ ከዚህም በላይ ሊናገር ቢችልም፣ ጸሐፊአችን ግን ንግግሩን በሦስት ዋና ክፍሎች በመክፈል ጠቅለል አድርጎ አቅርቦልናል፡ እያንዳንዱ አንጓ የሚጀምረው በመለኮታዊ በጎነት ሲሆን ለቃል ኪዳኑ ታማኝ ሆኖ መዝለቅን፣ እና ተያይዘው የሚመጡ ውጤቶችን ወይም ሁለቱንም በጣምራ አስከትሎ ይመጣል፡፡

*ኢያሱ 23፡2-8፡፡* የመጀመሪያው አንጓ፣ በ23፡2-8፣ እግዚአብሔር ለእስራኤል በጎነቱን በገለጠባቸው ሁለት ምሳሌዎች ይጀምራል፡፡ በቁጥር 3 ውስጥ፣ በድል አድራጊነት መውረስ የቻላችሁት “እግዚአብሔር አምላካችሁ ስለ እናንተ ስለተዋጋላችሁ ነው” በማለት ኢያሱ እስራኤልን ያሳስባል፡፡ በቁጥር 4 ደግሞ፣ እግዚአብሔር ራሱ “ኢነዚያን መንግሥታት ለዘላለም ርስት አድርጎ እንዳከፋፈላቸው ኢያሱ ያስታውሳቸዋል፡፡

ከዚያም ኢያሱ እስራኤል ለእግዚአብሔር አድናቆት በሞላበት መንገድ ታማኝ ሆና መዝለቅ እንደሚጠበቅባት ወደማሳሰቡ ይሸጋገራል፡፡ በቁጥር 6 ላይ “እስራኤል እንድትጠነክርና ሁሉን በሙሴ ህግ ላይ እንደተቀመጠው እንድትፈጽም” ኢያሱ ለእስራኤል ጥሪ ያቀርባል፡፡ እነዚህ ቃላት በኢያሱ 1፡7 ላይ እግዚአብሔር ለኢያሱ ከሰጠው ትዕዛዝ የተጠቀሱ ናቸው፡፡ እነዚህን የተለመዱ ቃላት ተከትሎ ግን፣ አንድ ለየት ያለ ታማኝነትን የሚጠይቅ አገልግሎት ጥሪ ሲቀርብ እናስተውላለን፡፡ በመጽሐፉ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ፣ እስራኤላውያንን የከነዓንን ጣዖታት እንዲያስወግዱ እና በጣዖታት ከረከሱ ከነዓናውያን ልምምዶች እንዲርቁ ኢያሱ ለእስራኤል ጥሪውን ያቀርባል፡፡ በቁጥር 7 ላይ “በእናንተ መካከል ወደ ቀሩት ወደ እነዚህ አሕዛብ አትግቡ የአማልክቶቻቸውንም ስም አትጥሩ፥ አትማሉባቸውም፥ አታምልኩአቸውም፥ አትስገዱላቸውም” ይላቸዋል፡፡ በማስከተል ደግሞ ኢያሱ በቁጥር 8 ላይ እንዲህ ይላቸዋል፡ “ወደ አምላካችሁ ወደ እግዚአብሔር ተጠጉ እንጂ።”

ኢያሱ ጣዖት አምልኮን አስመልክቶ ፍጹም ክልከላ የማድረጉ ነገር አዲስ አለመሆኑ መግለጫ የሚያስፈልገው ጉዳይ አይደለም፡፡ ከዐሥርቱ ትዕዛዛት የመጀመሪዎቹን ሁለቱን እና ከሃሰተኛ አማልክት አርካሽ ተፅዕኖ ነፃ እንዲሆኑ ከሚያስጠነቅቁ ከፔንታቱክ ምንባቦች በርካቶቹን መለስ ብሎ አስቃኝቷቸዋል፡፡ ጸሐፊአችን ግን ጉዳዩን በዚህ ስፍራ ሲያነሳው፣ ቀደም ባሉት ምእራፎች ላነሳቸው ወሳኝ ጉዳዮች በተለይ ይህኛው ጉዳይ ወሳኝ መሆኑን በግልጽ አስቀምጧል፡፡ በኢያሱ አመራር ዘመን እግዚአብሔር ለህዝበ እስራኤል ካደረገው ነገር የተነሳ፣ እስራኤላውያን ወደ ሌሎች አማልክ ዘወር ማለት ጨርሶ አይገባቸውም፡፡

*ኢያሱ 23፡9-13፡፡* በ23፡9-13 የሚገኘው ሁለተኛው የኢያሱ ንግግር አንጓ፣ የሚጀምረው ስለ እግዚአብሔር በጎነት በማውሳት ነው፡፡ በቁጥር 9 ውስጥ፣ “እግዚአብሔር ታላላቆችንና ኃይለኞችን አሕዛብ ከፊታችሁ አስወጥቶአል፤” በማለት ኢያሱ ያሳሰባቸው ሲሆን፣ በቁጥር 10 ደግሞ፣ አሁንም እንኳን “ስለ እናንተ የሚዋጋ እርሱ ነውና” ብሏቸዋል፡፡

ከዚያም በቁጥር 11፣ ልክ እንደ መጀመሪያው አንጓ፣ እስራኤል በታማኝነት ምላሽ እንድትሰጥ ኢያሱ ለእስራኤል ጥሪውን አቅርቧል፡፡ “እግዚአብሔር አምላካችሁን ውደዱ” በማለት ያሳሰባቸው ሲሆን፣ በዚህ ስፍራ ኢያሱ የጠቀሰው በዘዳግም 6፡5 ከትእዛዛት ሁሉ ትልቅ የሆነውን ትዕዛዝ ነው፡፡ ይህ በደንብ የምናውቀው ጥቅስ “አንተም አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹምም ኃይልህ ውደድ።” የሚል ነው፡፡ በዘዳግምም ሆነ በኢያሱ መጽሓፍት ውስጥ እግዚአብሔርን መውደድ ማለት ለእግዚአብሔር ብቻ ሁለንተናን መስጠትንና ለሌሎች አማልክት ፈጽሞ አለማሰብ ማለት ነው፡፡

ኢያሱ ግን በዚህኛው የንግግር አንጓው፣ አንድ እርከን ሄደት ይላል፡፡ ይህ ያልተከፋፈለ መሰጠት ምን ያህል ወሳኝ እንደሆነ ለማሳየት፣ ለእግዚአብሔር አለመታመን ሊያስከትልባቸው ስለሚችለው አስከፊ እርግማን ብርቱ ማስጠንቀቂያ ይሰጣቸዋል፡፡ በቁጥር 12 እና 13 እንደጠቀሰው፡ “እናንተ ግን ተመልሳችሁ በመካከላችሁ ወደ ቀሩት

*ወደ እነዚህ አሕዛብ ብትጠጉ፥ ከእነርሱም ጋር ብትጋቡ፥ እናንተም ወደ እነርሱ እነርሱም ወደ እናንተ ብትደራረሱ፥" ካለ በኋላ በመቀጠል "አምላካችሁ እግዚአብሔር ከሰጣችሁ ከዚህች ከመልካሚቱ ምድር እስክትጠፉ ድረስ መውደቂያና ወጥመድ፥ በጎናችሁም መግረፊያ፥ በዓይናችሁም እሾህ ይሆኑባችኋል" ብሏቸዋል፡፡* እግዚአብሔር ለእነርሱ እነዚያን የመሰሰሉ ተዓምራት ቢያደርግም፣ እስራኤላውያን ግን በተስፋዪቱ ምድር ውስጥ ያሉትን የከነዓናውያን መንገዶች የሚከተሉ ከሆነ በእግዚአብሔር አስከፊ ፍርድ ስር እንደሚወድቁ አስጠንቅቋቸዋል፡፡

በበርካታ ገጽታዎች፣ በእርግማኖች ላይ ልዩ ትኩረት የመስጠቱ ጉዳይ ያልተለመደ ነው፡፡ ዘጸአት 19፡4-6 በመሳሰሉት ምንባቦች ውስጥ፣ ወደፊት ስለሚገጥሟቸው በረከቶች ብቻ ተጠቅሰው ታገኛላችሁ፡፡ ዘዳግም 28 እና 30፡15-19 ባሉት ምንባቦች ደግሞ፣ በረከትና መርገም ጎን ለጎን ተቀምጠው እናገኛለን፡፡ ሆኖም በዚህኛው የኢያሱ ንግግር አንጓ ውስጥ የምናገኘው ግን ወደፊት ሊያገኛቸው የሚችለውን እርግማን ብቻ ነው፡፡

*ኢያሱ 23፡14-16፡፡* በኢያሱ ንግግር ሦስተኛ እርከን በ23፡14-16 ውስጥ፣ ኢያሱ በድጋሚ የሚጀምረው በእግዚአብሔር በጎነት ነው፡፡ በቁጥር 14 ውስጥ፣ "እግዚአብሔር ስለ እናንተ ከተናገረው ከመልካም ነገር ሁሉ አንድ ነገር እንዳልቀረ" ይህ ዐረፍተ-ነገር የተጠቀሰው ከ21፡45 ሲሆን፣ ጸሐፊአችንም ተመሳሳዩን ማረጋገጫ ይሰጣል፡፡ በዚህ ሦስተኛ እርከን ላይ ግን፣ ኢያሱ ለታማኝነት ጥሪ ማቅረቡን ይተውና ወዲውኑ በምትኩ የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን በመተላለፍ ስለሚመጣባቸው አስከፊ እርግማን ያስጠነቅቃቸዋል፡፡ በ23፡15 ውስጥ፣ "ከዚህች ከመልካሚቱ ምድር እናንተን እስኪያጠፉችሁ ድረስ እግዚአብሔር እንዲሁ ክፉን ነገር ሁሉ ያመጣባችኋል" ዘሌዋውያን 26 እና ዘዳግም 4፣ 28 የመሳሰሉ ክፍሎች እንደሚያስተምሩን፣ በእግዚአብሔር ላይ ማመጽ እስራኤልን ወደ ጥፋት እና ከተስፋዪቱ ምድር ወደ ግዞት መሄድን ያስከትላል፡፡

በእነዚህ አንጓዎች ውስጥ እያደገ የሄደውን ሃሳብ ስንመለከት በዚህ ንግግሩ የኢያሱ ተቀዳሚ ትኩረት ምን እንደሆነ ያመለክተናል፡፡ በመጀመሪያና ከሁሉ ይልቅ፣ የእግዚአብሔርን መልካምነት ካቃለሉ በእስራኤል ላይ ስለሚወርድባቸው እርግማን ሊያስጠነቅቃቸው ይፈልጋል፡፡ ግን ልብ ልንል የሚገባን፣ እነዚህ መቅሰፍቶች ይመጡባችኋል ብሎ የሚያስጠነቅቀው ትናንሽ ውድቀቶችን ሁሉ እየሰበሰበ አለመሆኑን ነው፡፡ በ23፡16 ውስጥ እስረኤልን እንዳስጠነቀቀው፣ "አምላካችሁ እግዚአብሔር ያዘዛችሁን ቃል ኪዳን ስታፈርሱ፥ ሄዳችሁም ሌሎችን አማልክት ስታመልኩ፥" ማፍረስ ተብሎ የተጠቀሰው ቃል አባር *abar* (עָבַר) የተሰኘውን የዕብራይስጥ ግስ ነው፡፡ ጸሐፊአችን ይህንን ቃል የሚጠቀመው እጅግ ለከፋና፣ አገርን በመክዳት እና ከጠላት ጋር ከማበር ጋር የሚስተካከሉትን ዓይነት ማለትም፣ በ7፡10፣ 15 አክዓን ካደረገው በደል ጋር የሚመሳሰሉትን ነው፡፡ ኢያሱ በልቡናው የነበሩት ጥቃቅን የንጽህና ጉድለቶች ወይም ቀላል ስህተቶች አይደሉም፡፡ ይልቁኑ፣ ማለት የፈለገው እጅግ የከፋውን አምልኮተ ጣዖት፣ ወይም በዚህ ስፍራ እንዳስቀመጠው፣ እጅግ አውዳሚ የሆነውን ሌሎች አማልክትን ማገልገልን ነው፡፡

> ***ከ23፡16 ምንባብ እንደምንረዳው ሌሎችን አማልክትን ለማገልገል ዘወር ማለት እንደሌለባቸው ህዝቡን አስጠንቅቋቸዋል፡፡ ስለዚህ፣ በዚህ ጉዳይ፣ የጌታን ቃል ኪዳን መተላለፍ ማለት የመጀመሪያዎቹን ሁለቱን ትእዛዛት መተላለፍ ማለት ሲሆን፣ ያም ቃል ኪዳን ማፍረስን ያስከትላል፡፡ ይህም፣ በዘሌዋውያን 26 ሙሴ ስለ ቃል ኪዳን በረከትና ስለ መርገም ለህዝቡ ማስጠንቀቂያ በሰጠበትና በዘዳግም 4፡25-31 እና ዘዳግም 28-32 ውስጥ በፍፁም እንዳያደርጉ ማሳሰቢያ የሰጠበት ነው፡፡ እናም ኢያሱ፣ አሳዳጊው፣ ሙሴ፣ ይሰጠው የነበረውን መመሪያ በመቀጠል ያቀርባል፡፡ ደግሞም ህዝቡን ይማጸናል፣ ተማፅኖውም ተሸግረው ወደ ምድሪቱ ገብተዋል ምድሪቱንም ወርሰዋል ስለዚህ ህግጋቱን ሊተላለፉ እና የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ሊያፈርሱ አይገባም፡፡ ስለዚህም ሙሴ ያስጠነቅቃል፡ ያንን ቢያደርጉ ግን፣ ከምድሪቱ በግዞት ይወሰዳሉ፡፡ በዚህም ምክንያት፣ ቃል ኪዳኑን በመጠበቅ በምድሪቱ ላይ ረጅም ዘመን እንዲኖሩ ኢያሱ ያሳሰባቸዋል፡፡***
>
> \- ***ዶ/ር ጀምስ ኤም፣ ሃሚልተን***

ኢያሱ የሰጠውን የቃል ኪዳን ማስጠንቀቂያ መሠረታዊ አወቃቀርና ይዘት በልቡናችን ይዘን፣ የዚህን ምዕራፍ ቀደምት ትርጓሜ ወደ መመልከቱ የምንሸጋገርበት እርከን ላይ ደርሰናል፡፡

## ቀደምት ትርጓሜ

በጥቅል አነጋገር፣ የኢያሱ መጽሐፍ ጸሐፊ ተደራሲያኑ በዚህ ምዕራፍ ከሚያስተላልፈው መልእክት እንዲያገኙ የሚፈልገው መልእክትና እንዲፈጠርባቸው የሚፈልገውን ተጽዕኖ መገመት አያዳግትም፡፡ በመሳፍንት ዘመን፣ እስራኤል የቅል ኪዳኑ ርግማን እንደደረሰባት እናስተውላለን ምክንያቱም ወደ ከነዓናውያን ጣዖታት ዘወር ብለው ስለነበር ነው፡፡ በነገሥታት ዘመንም፣ በተለያዩ ጊዜያት፣ በእስራኤል ላይ እጅግ የከፉ ነገሮችም መከሰት ጀመሩ ምክንያቱም በዓልንና ሌሎችን አማልክቶች ለማምለክ ራሳቸውን በመስጠታቸው ነበር፡፡ በእርግጥም ደግሞ፣ ልክ ኢያሱ እንደተናገረው፣ በስተመጨረሻም እስራኤላውያን ለባቢሎን ምርኮ ታልፈው ተሰጡ፡፡ ስዘሊህ፣ ተደራሲያኑ አሁን የደረሰባቸው አስቸጋሪ ሁኔታ የመጣው እግዚአብሔር ለህዝቡ ታማኝ ሆኖ መዝለቅ ስላልቻለ እንደሆነ እንዳያስቡ ይልቁኑ ጸሐፊአችን ለቀደምት ተደራሲያኑ የሚያሳስበው ችግሮቻቸው የመጡት ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆነው ሊዘልቁ ባለመቻላቸው እንደሆነ በግልጽ ይነግራቸዋል፡፡

ስላሉበት ሁኔታ እነርሱ ያለባቸውን ሃላፊነት ለማሳሰብ ሲል፣ ጸሐፊአችን በዚህ መጽሐፍ ስንመለከታቸው የቆዩትን የቃል አምስት ዋና መሪ ሃሳቦች ከቃል ኪዳን ማስጠንቀቂያዎቹ ጋር አዋህዶ ያቀርብልናል፡፡

### መለኮታዊ ሥልጣን

በመጀመሪያ ደረጃ፣ በኢያሱ ንግግሮች ውስጥ፣ ከጉባኤው በስተጀርባ ያለውን መለኮታዊ ሥልጣን ገልጧል፡፡ በ23፡2ሀ ውስጥ፣ ህዝቡን የሰበሰበው ኢያሱ እንደሆነ ይጠቅሳል፡፡ እንደምናውቀው፣ ጸሐፊአችን ደግሞ ደጋግሞ አጽንዖት እንደሰጠው ኢያሱ የሙሴ ባለሙሉ ሥልጣን ተተኪ እንዲሆን እግዚአብሔር ሥልጣን እንደሰጠው ጠቅሷል፡፡ ስለዚህ፣ ህዝቡን የሰበሰበው ኢያሱ እንደሆነ በመጥቀስ፣ ከዚያም ከቁጥር 2ለ - 16 በሚገኘውና ተከትሎ በሚመጣው የኢያሱ ንግግር ውስጥ፣ ከሁለቱም በስተጀርባ መለኮታዊ ሥልጣን እንዳለ ጸሐፊአችን አጽንኦት ሰጥቶበታል፡፡

ቀደም ብለን ፍንጭ እንደሰጠነው፣ የመጽሐፋችን ይህኛው ምዕራፍ የሚያነሳው ጉዳይ ከቀደምት ተደራሲያኑ መካከል አብዛኞቹ ለመቀበል የሚቸገሩበትን አመለካከት ነው፡፡  አሁን እየደረሰባቸው ያለው መከራ የደረሰባቸው ለቃል ኪዳን ታማኝ ባለመሆናቸው የመሆኑን ሃላፊነት አብዛኞቹ መቀበል አይፈልጉም፡፡ ስለዚህ፣ ጸሐፊአችን የቀደምት ተደራሲያኑን ቸልተኝነት የተጋፈጠው ኢያሱ ራሱ እነዚህን ቃላት እንደተናገራቸው በግልጽ በማስቀመጥ ነው፡፡

### የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን

በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ፣ በኢያሱ ንግግር ውስጥ የተገለጸው የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ለተሰኘው መሪ ሃሳብ የተሰጠ መሆኑ ነገር አስገራሚ አይሆንም፡፡ በ23፡4 ውስጥ፣ ጸሐፊአችን ከዮርዳኖስ መለስ ስላለው የእስራኤል "ርስት" ሲጠቅስ የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ጠቅሷል፡፡ እንደምታስታውሱት፣ "ርስት" ለሚለው ቃል የዕብራይስጡ አቻ "*nachalah*" (נַחֲלָה) የሚለው ሲሆን ይህም በመሃላ የተሰጠን ተስፋ፣ ማለትም ዘፍጥረት 15፡18 በመሳሰሉት ምንባቦች ውስጥ ለአባቶች ከተሰጠ ቃል ኪዳን ጋር የሚገናኝ ነው፡፡ በተጨማሪም በ23፡16 ውስጥ፣ ኢያሱ ንግግሩን ያጠቃለለው እስራኤላውያን "የአምላካችሁን የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን አታፍርሱ" በማለት እንደሆነ ማስታወስ ይገባናል፡፡

ጸሐፊአችን በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ላይ ያተኮረው ቀደምት ተደራሲኑ እግዚአብሔር ለእነርሱና ለአባቶቻቸው ያሳያቸውን በጎነቶች በማሰብ አድናቆታቸውን እንዲገልጹ ለማነሳሳት ነው፡፡ ያንን ካላደረጉ ግን የሚጠብቃቸውን የከፋ መለኮታዊ እርግማን ኢያሱ በጽኑ አሳስቧል፡፡

## የሙሴ ህግ ስነ-ልክ

በሦስተኛ ደረጃ፣ ኢያሱ ያቀረባቸው የቃል ኪዳን ማስጠንቀቂያዎች በበርካታ መንገዶች የመሴን ህግጋት ስነ-ልክ አስምረውባቸዋል፡፡ በኢያሱ ንግግር ውስጥ፣ በ23፡6 ላይ፣ "በሙሴ የህግ መጽሐፍ ውስጥ የተጻፈውን ሁሉ እንዲያደርጉ" እስራኤልን አዝዞአል፡፡ በ23፡11 ውስጥ ደግሞ፣ በዘዳግም 6፡5 ውስጥ ከተጠቀሰው የሙሴ ህግ በመጥቀስ "ጌታ አምላካችሁን ውደዱ" በማለት እስራኤልን አዝዞአል፡፡ በቁጥር 7 ውስጥ ደግሞ፣ "ከእነዚህ ህዝቦች ጋር አትደባለቁ" ደግሞም አማልክቶቻቸውን አታምልኩ በማለት ኢያሱ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ እነዚህና፣ በቁጥር 8 እና 12 ውስጥ የተገለጹትን መመሪያዎች ያወጣው ዘዳግም 7፡3 እና 10፡20 ከመሳሰሉት ምንባቦች ነው፡፡

ጸሐፊአችን ደግሞ ደጋግሞ በመጽሐፉ ውስጥ እንዳነሳው ኢያሱ የሙሴን ህግ ደጋግሞ የጠቀሰው ቀደምት ተደራሲያኑ ያላቸውን አመለካከት ከዚያ አንጻር ለማሳሰብ መሆኑን አሳስቧል፡፡ የእግዚአብሔርን በረከቶች ለመቀበል ያላቸው ብቸኛ ተስፋ ለሙሴ ህግጋት ያላቸውን ታማኝነት አትብቆ መጠበቅ ብቻ ነው፡፡

## የእግዚአብሔር ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይል

በአራተኛ ደረጃ፣ በኢያሱ የቃል ኪዳን ማስጠንቀቂያ ላይ ዘርዘር ያለ ማብራሪያ የሚሰጠው ይህ ምዕራፍ በእግዚአብሔር ልዕለ- ተፈጥሮአዊ ኃይል ላይም ትኩረት እንዲሰጥ አድርጓል፡፡ ለምሳሌ፣ በ23፡1 ውስጥ፣ ኢያሱ የጠራው ስብሰባ "እግዚአብሔርም እስራኤልን በዙሪያቸው ካሉት ጠላቶቻቸው ሁሉ ካሳረፈ በኋላ፥" የሚለውን ሐረግ በመጥቀስ የእግዚአብሔርን ታላቅ ኃይል አመልክቷል፡፡ ይኸው ተመሳሳይ መሪ ሃሳብ በኢያሱ ንግግር ውስጥ ደጋግሞ ተገልጧል፡፡ በ23፡3 ውስጥ፣ "ስለ እናንተ የተዋጋ እርሱ አምላካችሁ እግዚአብሔር ነው።" በማለት ኢያሱ እስራኤልን አሳስቧል፡፡ በቁጥር 5 ውስጥ፣ "አምላካችሁም እግዚአብሔር እርሱ ከፊታችሁ በብርቱ ይበትናቸዋል፥ ከፊታችሁም ያሳድዳቸዋል" በማለት ማረጋገጫ ሰጥቷዋል፡፡ ይህንኑ መሪ ሃሳብ በቁጥር 9 ውስጥ እንዲህ በማለት ደግሞታል "እግዚአብሔር ታላላቆችንና ኃይለኞችን አሕዛብ ከፊታችሁ አስወጥቶአል፤" በቁጥር 10 ደግሞ፣ "አምላካችሁ እግዚአብሔር እንደ ተናገራችሁ ስለ እናንተ የሚዋጋ እርሱ ነውና" ኢያሱ በተጨማሪም በእስራኤል ላይ የመጣውን ፍርድ ሲጠቅስም የእግዚአብሔርን ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይል አመልክቷል፡፡ በቁጥር 15 ውስጥ እንዳስቀመጠው፣ "እግዚአብሔር ከሰጣችሁ ከዚህች ከመልካሚቱ ምድር እናንተን እስኪያጠፋችሁ ድረስ እግዚአብሔር እንዲሁ ክፉን ነገር ሁሉ ያመጣባችኋል።" በቁጥር 16 ደግሞ "የእግዚአብሔር ቍጣ ይነድድባችኋል፥" በማለት ኢያሱ ያስጠነቅቃል፡፡

እንደምንመለከተው፣ የእግዚአብሔርን ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይል አስመልክቶ ኢያሱ እስራኤልን እንዳሳሰበ ጸሐፊአችን ደጋግሞ አመልክቷል፡፡ የኢያሱን ንግግሮች የጠቀሰው ቀደምት ተደራሲኑን ወደ አድናቆትና ወደ እግዚአብሔር በረከት ለማድረስ ነው፡፡ ደግሞም፣ በተመሳሳይ መንገድ፣ ባለመታዘዛቸው ምክንያት ሊደርስባቸው የሚችለውን መለኮታዊ እርግማን የጠቀሰውም ልባቸው እግዚአብሔርን በመፍራት እንዲነካና ወደ ንስሓ እንዲመጡ ለማድረግ ነው፡፡

## እስራኤል በጠቅላላ

በአምስተኛ ደረጃ ደግሞ፣ በምዕራፍ 23 የተቀመጠው የቃል ኪዳን ማስጠንቀቂያ በተጨማሪም እስራኤል በጠቅላላ የመሳተፉን ወሳኝነትም አመልክቷል፡፡ በቁጥር 2 ውስጥ በምናገኘው የኢያሱ ስብሰባ ውስጥ ኢያሱ መላውን እስራኤልን እንደሰበሰበ ተጠቅሷል፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን በመተላለፍ የሚመጣው እርግማን በጥቂት የእግዚአብሔር ህዝብ ላይ ብቻ የሚወርድ እንዳልሆነ ኢያሱ በንግግሩ አመልክቷል፡፡ የእስራኤል ህዝብ የወደፊት ዕጣ ፈንታ የሚወሰነው በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ኢያሱ ያወጃቸውን መርሆዎች በመጠበቃቸው ላይ ነው፡፡

የኢያሱ መጽሐፍ ጸሐፊ በምዕራፍ 23 ውስጥ ያነሳው ዋና መሪ ሃሳብ የሚያተኩረው ኢያሱ ለተናገረው ንግግር በእስራኤል ውስጥ ያለ ሰው ሁሉ ትኩረት እንዲሰጥ ለማድረግ እንደሆነ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ በኢያሱ ዘመን እንደነበረው ሁሉ፣

በጸሐፊአችን ዘመን የነበረው ጠቅላላ ህዝብ ለኢያሱ ማስጠንቀቂያ ጆሮውን ሊሰጥ ይገባል፡፡ የእግዚአብሔርን በረከት የመቀበል ተስፋቸው ተፈጻሚ የሚሆነው ያንን ካደረጉ ብቻ ነው፡፡

> **እስራኤላውያን ሊያደርጉና ላያደርጉ የሚገባቸውን ነገሮች አስመልክቶ ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ ነበር፡፡ እነርሱ ግን፣ ሌሎች አማላክቶችን ከሚያመልኩ እና እጅግ የከፉና የረከሱ ልምምዶችን ከሚያደርጉ ጎረቤቶቻቸው ጋር ተደበላልቀው ነበር፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር እስራኤላውያን ከእርሱ ጋር ላላቸው ቃል ኪዳን ታማኝ እንዲሆኑ ይፈልግ ነበር፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው ቃል ኪዳን ታማኝ ሆነው ከዘለቁ፣ ነገሮች ሁሉ መልካም እንደሚሆኑላቸው ተስፋ ሰጥቷቸዋል፡፡ ቃል ኪዳኑን ከተላለፉ ግን፣ ነገሮቻቸው እንደሚበለሻሹባቸው ነግሯቸዋል፡፡ በእኛም ሕይወት ይኸው ነገር በተመሳሳይ ሁኔታ ይፈጸማል፡፡ ለእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ታማኝ ብንሆን፣ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ይሆናል፣ ይመራናል፣ በኢያሱ መጽሐፍም ተስፋን እንደሰጠ በእኛ ሕይወት ውስጥ ሥራውን ይሠራል፡፡**
>
> \- **ፓስተር ማይካ ጉሳ**

የኢያሱ መጽሐፍ ኢያሱ የሰጣቸውን የቃል ኪዳን ማስጠንቀቂያዎች በመዘገብ እስራኤላውያን ለቃል ኪዳን ታማኝ ሆነው እንዲዘልቁ እንዳሳሰበ ከተመለከትን፣ አሁን ደግሞ በዚህ ትምህርታችን ሁለተኛ ወደሆነውና “የኢያሱ የቃል ኪዳን ተሃድሶ ክብረ-በዓል” ወደተሰኘው ርዕስ እንሸጋገራለን፡፡

# የቃል ኪዳን ተሃድሶ

በበርካታ መንገዶች፣ በምዕራፍ 23 ያለው ድራማ በጉጉት ልባችንን ይሰቅለዋል፡፡ እስራኤል ከእግዚአብሔር ጋር ያላትን ቃል ኪዳን ብታፈርስ ሊገጥማት የሚችለውን አሰቃቂ ነገር የሚያሳስብ የማስጠንቀቂያ ንግግር ኢያሱ አድርጓል፡፡ እስራኤል እንዴት ምላሽ እንደሰጠች የሚመለከት ፍንጭ ግን ግን የለም፡፡ ኢያሱ የሰጡትን ምላሽ የትኛውንም ዘገባ ሳያስቀምጥለን በማለፍ ተደራሲያኑን በምዕራፍ 24 ሊያነሳ ላሰበው ሃሳብ ማዘጋጀትን ምርጫው ያደርጋል፡፡ በዚህ የመጨረሻ ምዕራፍ ውስጥ፣ ኢያሱ ሁለተኛ ስብሰባ ይጠራል፡፡ በዚህ የቃል ኪዳን ተሃድሶ በዓል ላይ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ቃል ኪዳን ለማደስ ራሳቸውን እንደገና ይሰጣሉ፡፡ ይህም በዓል በተምሳሊትነት የሚያሳየው ቀደምት ተደራሲያኑ በኢያሱ መጽሐፍ ከተጠቀሰላቸው ነገር በመማር እንዴት ምላሽ ሊሰጡ እንደሚገባቸው ነው፡፡

ኢያሱ ያከናወነውን የቃል ኪዳን ተሃድሶ በዓል በተለመደው መንገድ እንመለከታለን፡፡ አወቃቀርና ይዘቱን ከዚያም ቀደምት ትርጓሜውን እንዳስሳለን፡፡ አስቀድመን የኢያሱን የቃል ኪዳን ተሃድሶ አወቃቀርና ይዘት እንመልከት፡፡

# አወቃቀርና ይዘት

እንደተመለከትነው፣ የእስራኤል ነገዶች በተለያዩ ርስቶቻቸው ላይ ከሰፈሩ በኋላ፣ ኢያሱ እንዲሰበሰቡ ጥሪ ያቀርባል፤ ስፍራው ምናልባትም በሴሎ ይሆናል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ግን፣ ሌላ ጉባዔ እናገኛለን፡፡ በዚህ ወቅት ስፍራው ሴኬም ነው፡፡ ሴኬም ለእስራኤላውያን የተቀደሰች ልዩ ስፍራ ናት፡፡ በዘፍጥረት 12፡7 እንደምናነብበው፣ አብርሃም በተስፋዪቱ ምድር ላይ የመጀመሪውን መሰዊያ ለእግዚአብሔር ያቀረበው በዚያን ስፍራ ነው፡፡ ሴኬም በገሪዛምና በኤባል ተራራ አቅራቢያ የምትገኝ ስፍራ ስትሆን፣ በዚያም ስፍራ ሙሴ በዘዳግም 11 እና 27 ውስጥ ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ቃል ኪዳን እንዲያድሱ ትዕዛዝ አስተላልፏል፡፡ በመጽሐፋችን በዚህ የመጨረሻ ምዕራፍ ውስጥ፣ ሴኬም ኢያሱ የእስራኤል መሪነት ሥራው የተደመደመበት ስፍራ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

በሴኬም የተከናወነው የእስራኤል የቃል ኪዳን ተሃድሶ ታሪክ ያለ ምንም ጥርጥር በአራት ዋና ክፍሎች ይከፈላል፡፡ በመጀመሪያ በ24፡1 ላይ፣ ኢያሱ ለጉባዔው ያቀረበውን የክስ መጥሪያ እናነብባለን፡፡ ይህ የክስ መጥሪያ በ24፡28 ውስጥ በተከናወነውና ኢያሱ ጉባዔውን በበተነበት ንግግር ውስጥ ሚዛኑን እንዲጠብቅ ተደርጓል፡፡ በእነዚህ በሁለቱ መካከል፣ ከቁጥር 2-24 ውስጥ ኢያሱ ያደረገውን ሁለተኛ ንግግርና የእስራኤልን ምላሽ የያዘው ትረካ ይመጣና ከቁጥር 25-27 የሚገኘውን ቃል ኪዳኑ የጸደቀበትን ዘገባ ያስከትላል፡፡ አስቀድመን በቁጥር 1 ውስጥ ያለውን የክስ ጥሪ እንመልከት፡፡

## የክስ መጥሪያ

በዚህ ስብሰባ ላይ ኢያሱ ያቀረበው ሙግት በምዕራፍ 23 ከቀረበው ሙግት ጋር ተመሳሳይነትም ልዩነትም ያለው ነው፡፡ ልክ እንዳለፈው ስብሰባ ሁሉ፣ በ24፡1 ውስጥ ኢያሱ "የእስራኤልን ነገዶች በጠቅላላ" ደግሞም "ሽማግሌዎችን፣ አለቆችን፣ መሳፍንትን፣ እና የእስራኤልን አለቆች" ሰበሰበ፡፡ በዚህኛው ስብሰባ የምናስተውለው ወሳኝ ልዩነት ኢያሱና እስራኤል "ራሳቸውን በእግዚአብሔር ፊት ማቅረባቸው" ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ፣ የተሰበሰቡት የእግዚአብሔር ክብር በግልጽ በሚታይበት በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ነው፡፡ ጸሐፊአችን በዘጸአት 19-24 ከተጠቀሱት ጋር እያዛመደ ከሚጠቅሳቸውና ከሚያሰምርባቸው ወሳኝ ክስተቶች መካከል ይህኛው ከብዙዎቹ የመጀመሪያው ነው፡፡ በእነዚህ ምዕራፎች፣ እሰስራኤላውያን በሲና ተራራ በገሃድ ከተገለጸው ከእግዚአብሔር ህላዌ ፊት ቃል ኪዳን ገብተው ነበር፡፡ ስለዚህ፣ ልክ እንደ ዘጸአቱ ሁሉ፣ በኢያሱ ዘመን የተደረገው የቃል ኪዳን ተሃድሶም የተከናወነው በእግዚአብሔር ገሃድ ህላዌ ነው፡፡

## ንግግሩና ምላሾቹ

ከኢያሱ ሙግቶች በኋላ፣ ጸሐፊአችን የሚሸጋገረው በምዕራፍ 24፡2-24 ወደሚገኘው የኢያሱ ንግግርና የእስራኤል ምላሽ ነው፡፡ በጥቅል አነጋገር፣ በዚህ ስፍራ ኢያሱ ያደረገው ንግግር በምዕራፍ 23 ስብሰባ ካደረገው ንግግር ጋር የሚስማማ ነው ምክንያቱም ንግግሩ የሚያተኩረው እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር ባደረገው ቃል ኪዳን መሠረታዊ ባህርያት ላይ ማለትም፡ በመለኮታዊ በጎነትላ ማተኮሩ፤ እስራኤል ለእግዚአብሔር ታማኝ እንድትሆን በሚያቀርበው ሙግት ላይ መሆኑና ለመታመን የሚያስከትለውን ዳፋ ያካተተ መሆኑ ነው፡፡ ልክ በምዕራፍ 23 እንደሆነው ሁሉ፣ ምዕራፍ 24 በጣዖት አምላኪነት ላይ ልዩ አትኩሮት ያደርጋል፡፡ ግን ካለፈወ ምዕራፍ በተለየ መንገድ፣ ይህ ምዕራፍ ኢያሱ ለተናገረው ነገር እስራኤላውያን የሰጡትን ምላሽ ይዘግባል፡፡

የዚህ ንግግር የመጀመሪያ አንጓ በ24፡2-13 የቀረበውን የመለኮታዊ በጎነት ቅኝት ሰፋ ያለ ስፍራ ሰጥቶታል፡፡ በምዕራፍ 23 ውስጥ፣ እግዚአብሔር ለእስራኤል ያደረጋቸውን በርካታ ነገሮች ኢያሱ ጠቅለል አድርጎ አቅርቧቸዋል፡፡ በዚህ ስፍራ ግን፣ የራሱን ቃላት ከመጠቀም ይልቅ፣ በቁጥር 2 ላይ ኢያሱ "የእስራኤል አምላክ፣ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል …" በማለት ይጀምራል፡፡ በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ፣ ኢያሱ የሚዘግበው በመገናኛው ድንኳን አጠገብ በነበረ ጊዜ እግዚአብሔር ራሱ በቃጥታ ሲናገር የሰማውን ነው፡፡ ወደ ዐሥራ ስምንት ለሚጠጉ ጊዜያት እግዚአብሔር ለእስራኤል ያደረገውን ነገር አንደኛ መደብን በመጠቀም "እኔ" በማለት ደጋግሞ አውጇል፡፡  ይህ የአንደኛ መደብ አመለካከት የሚያስተጋባው በሲና ተራራ የተገለጠውን የእስራኤልን ቃል ኪዳን ሲሆን የተዘገበውም ሙሴ በሲና ተራራ ከእግዚአብሔር የሰማውን በሚያቀርብበት ዓይነት ነው፡፡ ይህም ዓላማ ያደረገው እግዚአብሔር ራሱ ለእስራኤል ያደረጋቸውን በጎነቶች በቀጥታ በማሳሰብ ትኩረታቸውን መሳብ ነው፡፡

እግዚአብሔር በሦስት የተለያዩ የታሪክ ዘመናት ለእስራኤል ያደረገውን በጎነት ደጋግሞ አሳስቧል፡፡ በመጀመሪያ በቁጥር 3 እና 4 ውስጥ፣ ቀደም ባሉት የእስራኤል አባቶች ዘመን እግዚአብሔር እንዴት ለእስራኤል ሞገስን እንደሰጠ እግዚአብሄር አሳስቧል፡፡   ሁለተኛ፣ ከቁጥር 5-10 ውስጥ፣ በሙሴ ዘመን ያደረገውን በጎነት ጠቅሷል፡፡ ሦስተኛ ደግሞ፣ በቁጥር 11-13 ውስጥ፣ በኢያሱ ዘመን በህዝበ እስራኤል ምን እንደተከናወነ በመግለጽ ያጠናቅቃል፡፡ በቁጥር 12 ውስጥ፣ የእስራኤል ጠላቶች የተሸነፉት "በሰይፍህም በቀሥትህም" አይደለም በማለት  እግዚአብሔር ጉዳዩን ግልጽ ያደርገዋል፡፡  በቁጥር 13 ደግሞ፣ "ያልደከማችሁበትንም ምድር፥ ያልሠራችኋቸውንም ከተሞች ሰጠኋችሁ፥ ተቀመጣችሁባቸውም ካልተከላችኋቸውም ከወይንና ከወይራ በላችሁ" በማለት የሰጣቸውን አክሎ ይገልጻል፡፡ ዋናው ሃሳብ እጅግ ግልጽ ነው፡፡ በእግዚአብሔር ፊት የተሰበሰቡት እስራኤላውያን ያገኙት ስኬት ሁሉ የመጣው በእግዚአብሔር በጎነት ነው፡፡

> ***ይህ የቃል ኪዳን ተሃድሶ በዓል የእስራኤልን ልጆች ለማስተማር የሚኖረው ፋይዳ እጅግ ወሳኝ እንደሆነ እኔ አምናለሁ፡፡ የዚህም ነገር አንዱ ገጽታ ይህንን የመሰነባበቻ ንግግሩን የጀመረው በእስራኤል የታሪክ ዘመናት የተገለጸውን የእግዚአብሔርን ታማኝነት በመግለጽ ነው፡፡ ከአብርሃም አንስቶ ከዚያም በኋላ በሌሎች አባቶች የተከናወነውን በመዘርዘር ይዘግባል፡፡ ከዚያም ደግሞ እግዚአብሔር እስራኤልን***

*ወዳዳነበት ወደ ቀይ ባህር ልምምድ ይሸጋገራል፣ ከዚ ደግሞ በምድረበዳ ስለተገለጸው የእግዚአብሔር ታማኝነት ያወሳ ሲሆን፣ በመጨረሻም በፍጥነት በተስፋዪቱ ምድር እግዚአብሔር እንዴት ድልን እንደሰጣቸው በመናገር ወደ መደምደሙ ይሸጋገራል፡፡ የእግዚአብሔርን ታማኝነት ለሌሎች ከተደረጉ ክስተቶች ብቻ ሳይሆን እነርሱ ራሳቸው ጥቂቶቹን በማየት ያጣጣሙ ምስክሮች ናቸው፡፡ ስለዚህም ነጥቡ፣ እኔ እንደማስበው፣ ኢያሱ ለእነርሱ የተደረጉትን እነዚህን ሁሉ ታሪካዊ ትምህርቶች የሚያነሳው፣ የእግዚአብሔርን ታማኝነት ሊያሳስባቸው፣ ማለትም ከአብርሃም ዘመን ጀምሮ ለህዝቡ ያደረጋቸውን እና ወደፊትም ታማኝ ሆኖ እንደሚዘልቅ ማሳየት ሲሆን፤ ስለዚህ እነርሱም፣ ታማኝ ሆነው ሊዘልቁ ይገባቸዋል፡፡*

- ***ዶ/ር ቲ.ጄ. ቤትስ***

በኢያሱ ንግግር ሁለተኛ አንጓ ውስጥ፣ በቁጥር 14-24፣ ኢያሱ የእግዚአብሔርን መልካምነት ያነሳል ያንንም ያደረገው በዚህ ጉዳይ እንከን ከተገኘባቸው ሊመጣ የሚችለውን ቁጣ በማሳሰብ ታማኝ እንዲሆኑ ጥሪ ለማቅረብ ነው፡፡ ደግሞም፣ ሙሴ በዘጸአት 19 እና 24 ውስጥ፣ ህዝቡ ምላሽ እንዲሰጠው ኢያሱ ይጠብቃል፡፡ ይህም ክፍል በሦስት የምላሽ ጥሪዎችና ምላሾች ይከፈላሉ፡፡

*የመጀመሪያ ጥሪና ምላሽ፡፡* የመጀመሪያው ጥሪና ምላሹ የሚገኘው በቁጥር 14-18 ውስጥ ነው፡፡ በቁጥር 14 ውስጥ፣ "አሁንም እግዚአብሔርን ፍሩ፥ በፍጹምም በእውነተኛም ልብ አምልኩት፤" በማለት ኢያሱ እስራኤልን ያሳስባል፡፡ ወደዚህ ፍጻሜ ለመድረስ ሊወሰድ የሚገባው የመጀመሪያ እርምጃ እስራኤላውያን "አባቶቻችሁም በወንዝ ማዶ በግብፅም ውስጥ ያመለኩአቸውን አማልክት ከእናንተ አርቁ፥" የተባለውን ተቀብለው ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡ ይህንንም ተከተ፣ በቁጥር 15 ውስጥ፣ "የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ።" በማለት ይነግራቸዋል፡፡ በምዕራፍ 23 ውስጥ ኢያሱ ጣዖት አምላኪነትን አስመልክቶ ማስጠንቀቂያ ቢሰጥም፣ እስራኤላውያን ግን አሁንም በውስጣቸው ጣዖታትን አስቀምጠዋል፡፡ ስለዚህ አሁን፣ ኢያሱ እያሳሰበ ያለው ከየትኛውም የሃሰት አማልክት ራሳቸውን እንዲያነፁ እግዚአብሔር የሚጠብቅባቸው መሆኑን ነው፡፡ ኢያሱም ለዚህ ማሳሰቢያ ተምሳሊትነቱን የሚያሳየው በ24፡15 ውስጥ የሚገኙትንና ታዋቂ የሆኑትን "እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን።" የሚሉትን ቃላት በመናገር ነው፡፡

እግዚአብሔርን የማገልገሉ ጉዳይ ለኢያሱ እጅግ ወሳኝነት አለው ያንንም የምናስተውለው ማገልገል ብሎ የተጠቀመበት የዕብራይስጥ ቃል ***"abad" (עָבַד)*** በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ዐሥራ ስድስት ጊዜ ተጠቅሷል፡፡ ከቁጥር 16-18 ውስጥም፣ እስራኤላውያን እግዚአብሔርን ለማገልግል ያላቸውን ቁርጠኝነት በመግለጽ ኢያሱ ላቀረበው ጥሪ አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ በቁጥር 18 ውስጥ እንደምናነብበው፣ ህዝቡም "ስለዚህ እርሱ አምላካችን ነውና እግዚአብሔርን እናመልካለን።"

*ሁለተኛው ጥሪና ምላሹ፡፡* ሁለተኛው ጥሪና ምላሹ የሚገኘው ከቁጥር 19-22 ውስጥ ነው፡፡ በቁጥር 19፣ ኢያሱ "እርሱ ቅዱስ አምላክ ነውና፥ እርሱም ቀናተኛ አምላክ ነውና እግዚአብሔርን ማምለክ አትችሉም፤ መተላለፋችሁንና ኃጢአታችሁን ይቅር አይልም።" በማለት ኢያሱ ጉባኤውን ይሞግታል፡፡ ኢያሱ በዚህ ስፍራ እያለ ያለው እስራኤል ከዚህ በኋላ መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ማገልገል አይችልም ደግሞም እግዚአብሔርም መተላለፋቸውን ጨርሶ ይቅር አይልም አይደለም፡፡ ይልቁኑ፣ እያለ ያለው ጣዖቶቻችሁን እስካላስወገዳችሁ ድረስ እንደገና እግዚአብሔርን ማገልገልና የእግዚአብሔርን በረከት መቀበል አትችሉም ነው፡፡ ምንም እንኳን ከዚህ ቀደም የተሠሩትን በደሎች እግዚብሔር ታግሦ ቢያልፍም፣ ከዚህ በኋላ ግን ፈጽሞ አይታገስም፡፡ ኢያሱ በ24፡20 ላይ እንዳስጠነቀቀው፣ ጣዖታትን በማገልገላቸው ከገፉበት እጅግ አሰቃቂ ጥፋት ይከተላል ደግሞም እግዚብሔር፣ "መልካም ካደረገላችሁ በኋላ ተመልሶ ክፉ ነገር ያደርግባችኋል፥ ያጠፋችሁማል አላቸው።" ደስ ሚሰኘው፣ ህዝቡ ይህንን አስደንጋጭ ማስጠንቀቂያ ካደመጠ በኋላ፣ በ24፡21 ላይ፣ "እንዲህ አይሁን፤ ነገር ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን አሉት።"

ሦስተኛው ጥሪና ምላሹ፡፡ ሦስተኛው ጥሪና ምላሹ የሚገኘው በቁጥር 23 እና 24 ውስጥ ነው፡፡ በቁጥር 18፣ 21 እና 22 ውስጥ ኢያሱ ከህዝቡ አዎንታዊ ምላሽ ከተቀበለ በኋላ፣ በቁጥር 23 ውስጥ፣ ኢያሱ እንደተናገረው፣ ለእግዚአብሔር ያላቸውን ታማኝነት የሚያረጋግጡበት የመጀመሪው ውጫዊ ተግባር "አሁን እንግዲህ በመካከላችሁ ያሉትን እንግዶች አማልክት አርቁ፥ ልባችሁንም ወደ እስራኤል አምላክ ወደ እግዚአብሔር አዘንብሉ አላቸው።" እስራኤል ደግሞ በቁጥር 24 ውስጥ፣ "አምላካችንን እግዚአብሔርን እናመልካለን፥ ድምፁንም እንሰማለን።" በማለት ምላሽ ሰጡ፡፡

> *የኢያሱ መጽሐፍ የመዝጊያ ምዕራፎች፣ ምዕራፍ 23 እና 24፣ ለእግዚአብሔር በፍፁም ታማኝ የመሆንን አስፈላጊነት አስመልክቶ ኢያሱ ያደረገው ንግግር ተካትቷል፡፡ በዚያም ስፍራ በተለይ ኢያሱ የሰጠውን ማስጠንቀቂያ ታገኛላችሁ ያም አባቶቻቸው ከወንዝ ማዶና በግብጽ ምድር ያመለኳቸውን አማልክት አታምልኩ የሚል ነው፡፡ ይህም ነገር የሚያሳየው እስራኤላውያን አዘውትረው ሌሎችን አማልክቶች ወደማምለክ ዘወር የማለት አዝማሚያ እንዳላቸው ነው፡፡ ይህም የሚያሳየው መሠረታዊ የሆነውን የሰብዓዊ ፍጡር ልብ ህግ ሲሆን፣ ኤ. ደብሊዩ. ቶዘር የተባሉ ሰው ልባችን ጣዖታትን ወደማምለክ ያዘነብላሉ ብለዋል፡፡ ለያህዌ፣ ለእግዚአብሔር የሚቀርብ ፍጹም ታማኝነት ብቻ እስራኤልን ውጤታማ እንደሚያደርግ ኢያሱ ያውቅ ነበር፡፡ ስኬታማ መሆን ብቻ ሳይሆን፣ ባርኮቱን ሙላት ይቀበላሉ፤ ምክንያቱም መዝሙረ ዳዊት እንደሚነግረን፣ የአህዛብ አማልክት ሕይወት የሌላቸው፣ የሚያመልኩዋቸውንም እንደ እነርሱ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ እውነተኛና ሕያው የሆነው አምላክ አንድ እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት፣ እግዚአብሔር ለእነርሱ ታማኝ እንደሆነ ሁሉ እስራኤልም ለጌታ ፍጹም ታማኝ ሆነው መዝለቅ የወደፊት ሕይወታቸው፣ ብልጽግናቸው እና ተስፋቸው ብቸኛ ምንጭ ነው፡፡*
>
> - *ሬቨረንድ ሚካኤል ጄ. ግሎዶ*

## ቃል ኪዳኑን የማጽደቅ በዓል

ከኢያሱ ንግግርና ከእስራኤላውያን ምላሽ በኋላ፣ ትረካው ከቁጥር 25-27 ውስጥ በሚገኘው እስራኤል ለእግዚአብሔር ያላትን አዲስ መሰጠት እና ህጉን የማጽደቅ በዓል ወደ መዘገቡ ይሸጋገራል፡፡ ይህ አንዱ፣ የሚጀምረው "በዚያም ቀን ኢያሱ ከሕዝቡ ጋር ቃል ኪዳን አደረገ፥ በሴኬምም ሥርዓትና ፍርድ አደረገላቸው።" በቁጥር 26 ውስጥ፣ ኢያሱም "ታላቁንም ድንጋይ ወስዶ በእግዚአብሔር መቅደስ አጠገብ ከነበረችው ከአድባሩ ዛፍ በታች በማቆም" ቃል ኪዳኑን ለመጠበቅ ያላቸውን መሰጠት አጽንቶታል፡፡

በዚህ ስፍራ የተጠቀሰው የአድባር ዛፍ በዘፍጥረት 12፡6 ውስጥ የተጠቀሰውና በሴኬም የሚገኘው የሞሬ አድባር ዛፍ የተባለው መታሰቢያ ነው፡፡ ያም ስፍራ በከነዓን ምድር አብርሃም ለመጀመሪያ ጊዜ መሠዊያ ያቆመበት ስፍራ ነው፡፡ በእነዚህ ተከታታይ ትምህርቶቻችን እንደተመለከትነው፣ በኢያሱ መጽሐፍ ውስጥ ድንጋዮች በተደጋጋሚነት አገልግሎት ላይ የዋሉት ለመታሰቢያነት ነው፡፡ ለምሳሌ፣ በ4፡7 ውስጥ፣ ኢያሱ በጌልጌላ ለእስራኤል ነገዶች "የዘላለም መታሰቢያ" ይሆን ዘንድ ዐሥራ ሁለት ድንጋዮችን አቁሟል፡፡ በ22፡34 ውስጥ የምናገኘውና ከዮርዳኖስ ማዶ ያሉት ነገዶች ያቆሙት መሰዊያ "እግዚአብሔር አምላክ እንደ ሆነ ይህ በመካከላችን ምስክር ነው" የሚል ስያሜ ነበረው፡፡ በ24፡27 ደግሞ፣ "እግዚአብሔር አምላካችሁን የተዋችሁ እንደሆነ ይህ ድንጋይ ምስክር ይሆንባችኋል" በማለት ኢያሱ አብራርቶላቸዋል፡፡ በሚመጣው ትውልድ፣ እስራኤል ጣዖታትን ሁሉ በመካድ ከእስራኤል ጋር ፍጹም የሆነ ቃል ኪዳን የገባች መሆኑን መካድ እንዳይቻል ይህ ድንጋይ ምስክር ሆኖ ይቆማል፡፡ ይህንን ቃል ኪዳን መጠበቅ ቢሳናቸውና ያንን ተከትሎ በሚመጣው የእግዚአብሔር ፍርድ ተወቃሽ የሚሆኑት ራሳቸው ናቸው፡፡

## ስንብት

ከእነዚህ አሳዛኝ ክንውኖች በኋላ፣ የእስራኤል የቃል ኪዳን ተሃድሶ ዘገባ የሚደመደመው በቁጥር 28 ውስጥ በሚገኘው ኢያሱ ጉባኤውን ባሰነባተበት ክንውን ነው፡፡ ጸሐፊአችን ዘገባውን የሚያጠናቅቀው "ኢያሱም ሕዝቡን በእያንዳንዱ ወደ ርስቱ ሰደደ።" በሚል ማስታወሻ ነው፡፡ ይህ የትረካው አፈጻጸም ቀደምት ተደራሲያኑ ልብ ሊሉት የሚገባ አንድ ወሳኝ ጥያቄ ያስነሳል፡፡ ለመሆኑ እስራኤል ጣዖታትን በመካድ እግዚአብሔርን ብቻ የማገልገል ቃል ኪዳኗን ትጠብቅ ይሆንን? መጽሐፉ በሚደመደምበት በ24፡31 በሚገኘው የማጠቃለያ ቃል ውስጥ "ኢያሱ ባለበት ዘመን ሁሉ፥ ከኢያሱም በኋላ በነበሩት ለእስራኤልም ያደረገውን የእግዚአብሔርን ሥራ ሁሉ ባወቁት በሽማግሌዎች ዘመን ሁሉ፥ እስራኤል እግዚአብሔርን አመለኩ።" በማለት ጸሐፊአችን ዘግቦልናል፡፡ ሆኖም ግን ከመሳፍንት፣ ከሳሙኤልና ከነገሥታት መጻሕፍት እንደምንረዳው፣ እስራኤል ለጥቂት ጊዜያት ታማኝ ሆና ከዘለቀች በኋላ፣ ወደ ኋላ ላይ በመጣው ትውልድ ጣዖታትን ለመካድ ገብታ የነበረውን ቃል ኪዳን ደግማ ደጋግማ አፍርሳለች፡፡ የመጽሐፋችን ቀደምት ተደራሲያንም እነርሱ እያለፉባቸው ያሉት መከራዎች ከዚህ የተነሳ እንደሆነ አውቀው ነበር፡፡

የኢያሱን መጽሐፍ የቃል ኪዳን ተሃድሶ አወቃቀርና ይዘት በልቡናችን በማድረግ አሁን ደግሞ፣ ወደ ቀደምት ትርጓሜው መሸጋገር ይገባናል፡፡

# ቀደምት ትርጓሜ

በጥቅሉ፣ የኢያሱ የቃል ኪዳን ተሃድሶ እንድምታዎች ለቀደምት ተደራሲያኑ የሚኖራቸው ፋይዳ እጅግ ግልጽ ነው፡፡ ጸሐፊአችን የኢያሱን መጽሐፍ ጽፎ ባጠናቀቀት ወቅት፣ የእስራኤል ህዝብ አባቶቻቸው በኢያሱ ዘመን ገብተዋቸው የነበሩትን ቃል ኪዳኖች መጠበቅ ተስኖዋቸው ነበር፡፡ አለመታዘዛቸውንም ተከትለው የመጡት ጥፋቶችም እጅግ ግልጽና ዘግናኝ ናቸው፡፡ በእስራኤል ውስጥ የሚኖር የትኛውም ሰው አሁን እያለፍንበት ያለው የከፋ ስቃይ ለምን ደረሰብን ብሎ ቢጠይቅ፣ የገቡትን ቃል ኪዳን በገሃድ በማፍረሳቸው የእግዚአብሔር ፍርድ ሊወድቅባቸው የሚገባ መሆኑን ኢያሱ 24 ያብራራልናል፡፡

ቀደም ባለው ትምህርታችን እንደተመለከትነው የመጽሐፋችን ቀደምት ተደራሲያን ይኖሩ የነበረው አንድም በመሳፍንት ዘመን በሆነ ወቅት፣ አሊያም በነገሥታት ዘመን፣ ወይም ይሁዳ ወደ ባቢሎን በምርኮ በተወሰደበት ኋለኛ ዘመን ሳይሆን አይቀርም፡፡ ምንም ይሁን ምን፣ የእግዚአብሔር ህዝብ አሰቃቂ የሆነውን መከራ ወይም ቅጣት የሚቀበሉት በመጽሐፋችን ምዕራፍ 24 ውስጥ ኢያሱ ያደሰውን ቃል ኪዳን ሲያፈርሱ እንደሆነ እንገነዘባለን፡፡ በመሳፍንት ዘመን፣ በእስራኤል ውስጥ ይኖሩ የነበሩ በርካቶች ጣዖታትን በማምለክ ወጥመድ ውስጥ ወድቀው ነበር፡፡ በውጤቱም፣ በምድሪቱ ውስጥ የሚገኙ በርካታ አካባቢዎች በሽንፈትና ነጻ በመውጣት ቀለበት ውስጥ ይሽከረከሩ ነበር፡፡ በነገሥታቱም ዘመን፣ ጣዖት አምላኪነት ዘርፈ ብዙ ወደ ሆነ መከራ ውስጥ አስገብቷቸዋል፡፡ በሰሜናዊው መንግሥት፣ አሦራውያን ደግመው ደጋግመው ወረራ በመፈጸም በመጨረሻም ለሰማርያ መውደቅና አብዛኛው ህዝብም በግዞት ለመወሰዱ ምክንያት ሆኗል፡፡ ቆየት ብሎም፣ በደቡቡ መንግሥትም የጠከሰተው ጣዖት አምልኮ የኢየሩሳሌምን ውድቀትና የባቢሎን ምርኮን አስከትሏል፡፡ በእነዚህ ጊዜያቶች ሁሉ ውስጥ፣ ታማኝ የሆኑት እስራኤላውያን ይቅርታን ሊያገኙና የእግዚአብሔርን በረከቶች ሊቀበሉ የሚችሉባቸውን መንገዶች እንዴት ሊያገኙ እንደሚችሉ በናፍቆት ይጠባበቁ ነበር፡፡ በዚህ ረገድ ኢያሱ 24 መመሪያ ይሰጣል፡፡ መመሪያውም፣ እስራኤላውያን እግዚአብሔር ያደረገላቸውን በርከታ በጎነቶች በማሰብ ከእርሱ ጋር የገቡትን ቃል ኪዳን ሊያድሱ ይገባቸዋል የሚል ነው፡፡ ይህንንም ሊያደርጉ የሚገባው ልክ በኢያሱ ዘመን የነበሩ እስራኤላውያን እንዳደረጉት ሁሉ እነርሱም አንዱንና ብቸኛውን አምላክ ለማገልገል ራሳቸውን በፍጹምነት በመስጠት ብቻ ነው፡፡

ጸሐፊአችን ቀደምት ተደራሲኑን ወደ ተግባራዊ ምላሽ ለማምጣት ያስቻለው ዘንድ ደጋግሞ ሲያነሳቸው የነበሩትን አምስት መሪ ሃሳቦች በዚህኛው የቃል ኪዳን ተሃድሶ ምዕራፍም ያነሳቸዋል፡፡

## መለኮታዊ ሥልጣን

በመጀመሪያ ደረጃ፣ ይህ ተሃድሶ በመለኮታዊ ሥልጣን የታጀበ መሆኑን በግልጽ አስቀምጦታል፡፡ ልክ እንደ ምዕራፍ 23 ሁሉ፣ በ24፡1 የሚገኘውም ስብሰባ ኢያሱን በስም ይጠቅሰዋል፡፡ ያንንም ያደረገው እግዚአብሔር ሥልጣን የሰጠው መሪ የዚህ በዓል ዋና ተዋናይ መሆኑን ማሳየት ነው፡፡ በተጨማሪም፣ በ24፡2 የሚገኘው የኢያሱ ንግግርና የእስራኤል ምላሽ የሚጀምረው "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦" በሚሉት ቃላት ነው፡፡ በዚህ ምዕራፍ የሚከናወኑት ተግባራት በእግዚአብሔር በራሱ ሥልጣን የታጀበ መሆኑን እነዚህ የመግቢያ ቃላት የትኛውንም ጥርጣሬ ያስወግዳሉ፡፡ ከዚህም ባሻገር፣ ጸሀፊአችን በዘገባው ደግሞ ደጋግሞ የኢያሱን ንግግር በመጥቀስ የሚያሳየን ነገር፣ እግዚአብሔር የሾመው ባለሥልጣን ኢያሱ ራሱ ለዚህ ጉባኤ ንግግር ማድረጉን ለማሳየት ነው፡፡

በዚህ ምዕራፍ ወደምናገኘው መለኮታዊ ሥልጣን አትኩሮትን ለመሳብ ሲል፣ በቀደምት ተደራሲያኑ ውስጥ ሚገኝ እያንዳንዱ ሰው ለየት ያለ ትኩረት እንዲሰጠው ጸሐፊአችን ጥሪውን ያቀርባል፡፡ ኢያሱ ያካሄደውን የቃል ኪዳን ተሃድሶ ቸል በማለት በራሳቸው መንገድ ከተጓዙ፣ በእግዚአብሔር ሥልጣን ላይ ማመጻቸው እንደሆነ ጸሐፊአችን ማሳሰቢያውን ያቀርባል፡፡

## የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን

በሁለተኛ ደረጃ፣ በዚህ የቃል ኪዳን ተሃድሶ ዘገባ ውስጥ፣ ኢያሱ ደግሞ ደጋግሞ ያነሳውና ማጣቀሻ ያደረገው የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳነ ነው፡፡ የእርሱ ንግግርና እስራኤላውያን የሰጡት ምላሽ የመለኮታዊ በጎነትን ገጽታዎች፣ ከሰው የሚጠበቀውን ታማኝነትና ያለመታዘዝን ዳፋ ያካተተ ነው፡፡ ከዚህም ባሻገር፣ ኢያሱ ባካሄደው ቃል ኪዳን የማጽናት በዓል፣ ጸሐፊአችን በ24፡25 ውስጥ "በዚያም ቀን ኢያሱ ከሕዝቡ ጋር ቃል ኪዳን አደረገ፥" በማለት በግልጽ አስቀምጦታል፡፡ ጸሐፊአችን በተጨማሪም እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር ያደረገውን ቃል ኪዳን ስብሰባውን ባሰናበተበት ወቅትም አንስቶታል፡፡ በቁጥር 28 ውስጥ፣ "ኢያሱም ሕዝቡን በእያንዳንዱ ወደ ርስቱ ሰደደ።" በማለት እንደገና "*nachalah*" (נַחֲלָה) የተሰኘውን የዕብራይስጥ ቃል ይጠቀማል፡፡

እንግዲህ፣ እንደተመለከትነው፣ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተጠቀሰው የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን መሪ ሃሳብ የሚያተኩረው በእግዚአብሔር በጎነትና ታማኝነት አስፈላጊ መሆኑን በማመልከቱ ላይ ነው፡፡ ቀደምት ተደራሲያኑ የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ምን ያህል እንዳፈረሱ በግልፅ እንዲያስተውሉለት ጸሐፊአችን ተስፋ ያደርጋል፡፡ ደግሞም ከእግዚአብሔር ጋር የገቡትን ቃል ኪዳን ለመጠበቅ ቃል ኪዳናቸውን እንዲያድሱም ጥሪውን ያቀርብላቸዋል፡፡ በንስሓ ካልተመለሱና ካልታደሱ በስተቀር እነርሱና ልጆቻቸው ከቃል ኪዳኑ ጋር የተያያዙት እርግማኖች በላያቸው ላይ መውረዳቸውን ይቀጥላሉ፡፡

## የሙሴ ሕግጋት ስነ-ልክ

በሦስተኛ ደረጃ፣ በምዕራፍ 24 የሚገኘው የኢያሱ የቃል ኪዳን ተሃድሶ ለሙሴ ህግ ስነ-ልክ እውቅናን ይሰጣል፡፡ ለምሳሌ፣ በቁጥር 14 እና 15 ውስጥ ኢያሱ ባደረገው ንግግርና እስራኤል በሰጠው ምላሽ ውስጥ "አባቶቻችሁም በወንዝ ማዶ በግብፅም ውስጥ ያመለኩአቸውን አማልክት" ደግሞም "የአሞራውያንን አማልክት" (አሞራውያን የከነዓናውያን ተለዋጭ ስም ነው) እንዲያስወግዱ ጥሪ ያቀርባል፡፡ ይህ መመሪያ መሠረት ያደረገው ዘዳግም 11፡28 በመሳሰሉ ምንባቦች ውስጥ በተጠቀሰው የሙሴ ህግ ጣዖታትን አታምልኩ የሚለውን ክልከላ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ፣ በቁጥር 19 ውስጥ ኢያሱ፣ "እርሱ ቅዱስ አምላክ ነውና፥ እርሱም ቀናተኛ አምላክ ነውና" በማለት ሲያውጅ፣ ኢያሱ የጠቀሰው በዘዳግም 20፡5 ከተጠቀሰው ከፔንታቱኩ ክፍል ውስጥ ነው፡፡ ጸሐፊአችን በቀደምት ተደራሲያኑ ውስጥ ምንም ዓይነት ጥርጣሬ ሊተው አልወደደም፡፡ የእግዚአብሔር በረከት ለመቀበል ተስፋ የሚደርጉ ከሆነ የሙሴን ህግ ስነ-ልክ ሊያከብሩ ይገባቸዋል፡፡

**የእግዚአብሔር ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይል**

በአራተኛ ደረጃ፣ በቃል ኪዳን ተሃድሶ ላይ የሚያተኩረው ይህ ምዕራፍ በተጨማሪም የእግዚአብሔርን ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይል ያረጋግጣል፡፡ ጸሐፊአችን ይህንን በግልጽ ያስቀመጠው በኢያሱ ንግግርና እስራኤል በሰጠበት ክፍል ውስጥ ሲሆን ያንንም ያሳየው እግዚአብሔር ለእስራኤል ስለ ገለጠው በጎነቱ የተናገረውን ኢያሱ ዘገባ ሲያቀርብ ነው፡፡ በቁር 3-6ሀ፣ እግዚአብሔር በአንደኛ መደብ ለእስራኤል ያደረጋቸውን ነገሮች ዘርዝሮ ተናግሯል፡፡ ለምሳሌ፣ በቁጥር 3፣ "አባታችሁንም አብርሃምን ከወንዝ ማዶ ወስጄ በከነዓን ምድር ሁሉ መራሁት፤ ዘሩንም አበዛሁ፥" ብሏል፡፡ በቁጥር 5 ደግሞ፣ "ግብፅን ቀሠፍሁ፤" ብሏል፡፡ ከቁጥር 6ለ-7፣ እግዚአብሔር ለእስራኤል ስላደረገው ነገር ኢያሱ የራሱን ማብራሪያ ሰጥቶበታል፡፡ በቁጥር 7፣ ግብፃውያን እስራኤላውያንን ወደ ባህሩ ያሳደዱበትን ታሪክ በማንሳት "ባሕሩንም መለሰባቸው፥ አሰጠማቸውም፤" በማለት ኢያሱ በተዛምዶ አቅርቦታል፡፡ ከቁጥር 8-13 ደግሞ፣ ምንባቡ ወደ አንደኛ መደብ ይመለሳል፡፡ በቁጥር 8፣ እግዚአብሔር "ወደ አሞራውያን ምድር አመጣኋችሁ፤ ... አሳልፌም በእጃችሁ ሰጠኋችሁ፥ ... ከፊታችሁም አጠፋኋቸው።" በቁጥር 12 ደግሞ፣ የከነዓንን ምድር ከመውረስ አንጻር፣ እግዚአብሔር ለእስራኤል፣ "በሰይፍህም በቀሥትህም ሳይሆን" በማለት የድሉን ኃይል አሳይቷቸዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ፣ እስራኤል ለኢያሱ ንግግሮች የሰጠው ምላሽ በእግዚአብሔር ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይል ላይ አተኩሯል፡፡ በቁጥር 17፣ "በዓይናችንም ፊት እነዚያን ታላላቅ ተአምራት ያደረገ፥" እና "በሄድንባትም መንገድ ሁሉ ባለፍንባቸውም አሕዛብ ሁሉ መካከል የጠበቀን፥" በማለት ህዝቡ በግብጽ ምድር ያደረገላቸውን መስክረዋል፡፡ በቁጥር 18 ደግሞ፣ "እግዚአብሔር አሕዛብን ሁሉ፥ በምድሪቱም የተቀመጡትን አሞራውያን ከፊታችን አሳደደ፤" በማለት ስምምነታቸውን ገልጸዋል፡፡ ኢያሱ ግን በቁጥር 20፣ "እግዚአብሔርን ትታችሁ እንግዶችን አማልክት ብታመልኩ፥ መልካም ካደረገላችሁ በኋላ ተመልሶ ክፉ ነገር ያደርግባችኋል፥ ያጠፋችሁማል አላቸው።"

እነዚህ የእግዚአብሔር ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይል አዋጆች ቀደምት ተደራሲያኑን የሚያሳስቡት ስለሚያገለግሉት አምላክ ማንነት ነው፡፡ እርሱ የኃይል ሁሉ አምላክ መሆኑን ጨርሶ መዘንጋት የለብንም፡፡ ለመባረክም ሆነ ለመርገም ያለው ችሎት ከምናስበው በላይ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት፣ ለእርሱ ቃል ኪዳን ታማኝ ሆነው ሊዘልቁ ይገባቸዋል፡፡

> ***እግዚአብሔር ከህዝበ እስራኤል ጋር ያለውን ግንኙነት ስንመለከት፣ ገሃድ ሆኖ የሚታየው ነገር እግዚአብሔር ልዕለ-ተፈጥሮአዊ በሆነ መንገድ ደግሞ ደጋግሞ ይባርካቸው እንደነበር ነው፡፡ ከዚያም ጀርባ አንድ እውነተኛ ዓላማ አለ ያም ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ግንኙነት አጥብቀው እንዲይዙና ለቃል ኪዳኑም ታማኝነታቸውን እንዲያረጋግጡ የሚያስላቸው ነው፡፡ በእነርሱ ላይ የሚያፈስሳቸው ልዕለ-ተፈጥሮአዊ በረከቶች፣ እኔ እንደማስበው፣ ሰዎች ወደፊት በሚመጡ ዘመናት የሚወድደን እግዚአብሔር፣ ስለ እኛ የሚጠነቀቅ እግዚአብሔር፣ እኛ ፈጽሞ የማይተወን ወይም የማይተወን አምላክ ነው ስለዚህ እኛም ከእግዚአብሔር በተቀበልነው ፍቅር ምክንያት፣ መለስ ብለን እርሱን ልንወድድ ደግሞም ከእርሱ ጋር ያለንን ግንኙነት በታማኝነት ልንቀጥል ይገባናል በማለት እንዲያስቡትና እንዲያስታውሱ ለማድረግ ነው፡፡***
>
> \- ***ዶ/ር ዳን ላቺክ***

**እስራኤል በጠቅላላ**

በመጨረሻም፣ በአምስተኛ ደረጃ፣ የኢያሱ የቃል ኪዳን ተሃድሶ የሚጀምረውና የሚጠናቀቀው እስራኤል በጠቅላላ የመሳተፏን ወሳኝነት በማመልከት ነው፡፡ በቁጥር 1 ውስጥ በሚገኘው በኢያሱ የመክፈቻ ንግግር ውስጥ "የእስራኤልን ነገድ ሁሉ ወደ ሴኬም ሰበሰበ፥ የእስራኤልንም ሽማግሌዎች አለቆቻቸውንም ፈራጆቻቸውንም ሹማምቶቻቸውንም"

እንደተገኙ ያመለክታል፡፡ ዘገባው የሚጠናቀቀውም በቁጥር 28 "ኢያሱም ሕዝቡን በእያንዳንዱ ወደ ርስቱ ሰደደ።" በማለት ነው፡፡

መላው እስራኤል በጠቅላላ በስብሰባው ላይ ተገኙ፣ ቃል ኪዳናቸውን አደሱ፣ ከዚያም እግዚአብሔር በሰጣቸው ርስት ለመስፈር ሄዱ፡፡ ጸሐፊአችን ለቀደምት ተደራሲኑ ያነገበው ዓላማ ግልጽ ነው፡፡ ይህ ጉዳይ በኢያሱ ዘመን እውነት በመሆኑ ምክንያት፣ ቀደምት ተደራሲያን በሆኑት መካከል የሚገኝ የትኛውም ሰው በዘመኑ ቃል ኪዳኑን አድሶ ሊመላለስ ይገባዋል፡፡

ስለ ቃል ኪዳን ተሃድሶ በተነጋገርንበት በዚህ ትምህርት፣ ለመጽሐፈ ኢያሱ ተቀዳሚ ተደራሲያን፣ የቃል ኪዳን ማስጠንቀቂያዎችን ወሳኝነት፣ እና የቃል ኪዳን ተሃድሶ የሚኖረውን ትልቅ ፋይዳ ስንመለከት ቆይተናል፡፡ አሁን ደግሞ ወደ ትምህርታችን ሦስተኛ ዋና ርዕስ፣ የመጽሐፋችንን ክርስቲያናዊ ተዛምዶ ወደምንመለከትበት ክፍል እንሸጋገራለን፡፡ ዛሬ እኔና እናንተ እንደ ክርስቶስ ተከታዮች እነዚህን ጉዳዮች በሕይወታችን እንዴት ተግባራዊ ልናደርጋቸው እንችላለን? ብለን መጠየቅ ይገባናል፡፡

## ክርስቲያናዊ ተዛምዶ

ይህ የመጽሐፋችን የመጨረሻ ዋና ክፍል ለቀደምት ተደራሲያኑ ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው የቃል ኪዳን ገጽታዎች እንዲያስተውሉ፣ በተለይ ደግሞ ታማኝ ሆኖ ለመዝለቅ የሚጠበቅባቸው ሃላፊነት እና ታማኝነታቸውን ቢያፈርሱ ደግሞ ሊመጣባቸው የሚችለውን እርግማን አስመልክቶ ጥሪውን ያቀርባል፡፡ ኢያሱ ራሱም እግዚአብሔር ከአብርሃምና ከሙሴ ጋር የነበረውን ቃል ኪዳን በልቡናው ይዟል፡፡ ቆየት ብለው የመጡት ብሉይ ኪዳን ተደራሲያንም እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር ያደረገውን ቃል ኪዳን ሊያስቡት ይገባቸዋል፡፡ ለእግዚአብሔር ቃል ኪዳን የተሰጠው አጽንዖት በእኛ ዘመን አግባብነት የሚኖረው እንዴት ነው?

እኛ እንደ ክርስቲያኖች፣ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት በተቀዳሚነት ሊገዛ የሚገባው ነቢዩ ኤርምያስ፣ ኢየሱስና የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች "አዲስ ኪዳን" ብለው በሚጠሩት መርህ መሠረት ነው፡፡ እንደ አለመታደል ሆኖ ግን፣ በርካታ ቅን የክርስቶስ ተከታዮች አዲስ ኪዳንን የሚረዱት ይህንን የኢያሱን መጽሐፍ ክፍል ከክርስቲያናዊ አኗኗር ጋር ለማጣጣም አዳጋች በሆነ መንገድ ነው፡፡ ስለዚህ፣ ለጥቂት ደቂቃዎች ቆም ብለን ኤርምያስ ስለ አዲስ ኪዳን ምን እንዳመለከተና የአዲስ ኪዳን ጸሓፍትም በክርስቶስ ፍጻሜውን ማግኘቱን እንዴት እንደተገነዘቡት መመልከት ይገባናል፡፡

> ነቢዩ ኤርምያስ በኤርምያስ 31፡31-32 ውስጥ ምን እንደተናገረ እስኪ እናድምጥ፡
>
> እነሆ፥ ከእስራኤል ቤትና ከይሁዳ ቤት ጋር አዲስ ቃል ኪዳን የምገባበት ወራት ይመጣል፥ ይላል እግዚአብሔር፤
> ከግብጽ አገር አወጣቸው ዘንድ እጃቸውን በያዝሁበት ቀን ከአባቶቻቸው ጋር እንደ ገባሁት ያለ ቃል ኪዳን አይደለም፤ እነርሱ በኪዳኔ አልጸኑምና፥ እኔም ቸል አልኋቸው፥ ይላል እግዚአብሔር፡፡

ይህ ምንባብ ከባቢሎን ምርኮ በኋላ እግዚአብሔር ከእስራኤል ቤትና ከይሁዳ ቤት ጋር የሚገባውን አዲስ ኪዳን ወይም (የታደሰ ቃል ኪዳን ተብሎ ሊተረጎም ይችላል) ነው የሚያውጀው፡፡

ኤርምያስ አብዛኛውን የአገልግሎት ዘመኑን ያሳለፈው ይሁዳ በባቢሎናውያን እጅ ስለሚደርስባት ግዞትና በሽንፈትም ስለምትቀበለው መከራ በማወጅ ነው፡፡ በኤርምያስ 31 ግን፣ "ወራት ይመጣል" በማለት ማወጅ ይጀምራል፡፡ በዚህ ምዕራፍ በሆነ ስፍራ "ወራት ይመጣል" የሚለው መግለጫ የሚያመለክተው ከባቢሎነ ምርኮ በኋላ የእግዚአብሔር ባርኮት በእስራኤል ላይ የሚፈስስበትን ወቅት ነው፡፡

እንግዲህ፣ ይህ አዲስ ኪዳን እግዚአብሔር በሙሴ ዘመን ከአባቶቻቸው ጋር እንዳደረገው ቃል ኪዳን ዓይነት አለመሆኑን ማስታወስ መልካም ነው:: በኢያሱ 23 እና 24 እንዳየነው፣ እስራኤላውያን በግልጽ የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ካቃለሉና ወደ ጣዖታት ዘወር ካሉ፣ የመከራን ስቃይ የሚጎነጩ ሲሆን ከተስፋዪቱ ምድር በግዞት የሚወሰዱበትም ዘመን ይመጣባቸዋል::

በሚያሳዝን ሁኔታ፣ እስራኤል ከእግዚአብሔር ጋር ያላትን ቃል ኪዳን አፈረሰች ከዚህም የተነሳ በመቶዎች ለሚቆጠሩ ዓመታት በአህዛብ መንግሥታት ጭቆና ስር ወደቁ:: ኤርምያስ ግን ለእስራኤል ተስፋ ይሰጣል፣ ያም ከምርኮ በኋላ፣ እግዚአብሔር እንደሚምራቸውና አዲስ ኪዳን እንደሚሰጣቸው ነበር:: በኤርምያስ 31፡33-34፣ ይህ አዲስ ኪዳን በሙሴ እንደተሰጠው ኪዳን በውድቀት እንደማይጠናቀቅ እግዚአብሔር ማረጋገጫ ሰጣቸው:: እንዲህ ይነበባል፡

> ከእነዚያ ወራት በኋላ ከእስራኤል ቤት ጋር የምገባው ቃል ኪዳን ይህ ነውና፥ ይላል እግዚአብሔር፤ ሕጌን በልቡናቸው አኖራለሁ፥ በልባቸውም እጽፈዋለሁ፤ እኔም አምላክ እሆናቸዋለሁ እነርሱም ሕዝብ ይሆኑኛል።
> እያንዳንዱ ሰው ባልንጀራውን፥ እያንዳንዱም ወንድሙን፦ እግዚአብሔርን እወቅ ብሎ አያስተምርም፤ ከታናሹ ጀምሮ እስከ ታላቁ ድረስ ሁሉ ያውቁኛልና፥ ይላል እግዚአብሔር:: በደላቸውን እምራቸዋለሁና፥ ኃጢአታቸውንም ከእንግዲህ ወዲህ አላስብምና። (ኤርምያስ 31፡33-34)

እነዚህ ጥቅሶች እንደሚያብራሩልን አዲሱ ኪዳን አይወድቅም ምክንያቱም እግዚአብሔር ህዝቡን ሙሉ በሙሉ ስለሚለውጥ ለእርሱ ታማኝ ሆነው መዝለቅ የሚችሉበትን አቅም ስለሚሰጣቸው ነው:: "ሕጌን በልቡናቸው አኖራለሁ፥ በልባቸውም እጽፈዋለሁ፤" ብሎ ተናግሯል::

ዘዳግም 30፡10 የመሳሰሉት ምንባቦች እንደሚያሳዩን፣ በእግዚአብሔር ህግ የተቃኘ ልብ፣ ዘወትር ለእግዚአብሔር ህዝብ ዓይነተኛ መለያ ነው:: ደግሞም፣ በእግዚአብሔር ጸጋ፣ ወደዚህ ዓይነተኛ መለያ ልባቸውን ሚያቀኑ የእስራኤል ቅሬታዎች ዘወትር ይኖራሉ:: ኤርምያስ 31 እንደሚያሳየን፣ አዲሱ ኪዳን ወደ ሙላቱ ሲደርስ፣ መንፈሳዊ ተሃድሶ ወደ ሙላት ይመጣል:: ይህም በጥቂቶች ላይ ብቻ ሳይሆን፣ የእግዚአብሔር ህዝብ ተብሎ በሚቆጠር በእያንዳንዱ ሰው ሁሉ ላይ ይሆናል::

በዚህ ስፍራ በኢያሱ ዘመን ከነበረው ጋር የሚቃረን ነገር እናስተውላለን:: አዲሱ ኪዳን ወደ ሙላቱ ሲደርስ፣ የእግዚአብሔርን ህዝብ ለእግዚአብሔር ታማኝ ሁኑ ብሎ ጥሪ ማቅረብ አስፈላጊ ሆኖ አይገኝም ማለት ነው:: ሁሉም በፍጹም ለእግዚአብሔር ታማኝ ይሆናሉ:: "እግዚአብሔር በደላቸውን ይምራቸዋል፣ ኃጢአታቸውንም አያስብም::"

> ***በኤርምያስ የተነገረው ተስፋና በሕዝቅኤል የተነገረው ተስፋ የሚያረጋግጥልን እግዚአብሔር ህጉን በልቡናችን እንደሚጽፍና በመንገዶቹም እንድንሄድ እንደሚያስችለን፣ መንፈሱን በውስጣችን እንደሚያኖር፣ ኃጢአታችንንም ይቅር እንደሚል ነው:: እናም፣ አዲሱም ኪዳን እንደ አሮጌው ኪዳን ሁሉ በደም ሊጸና ይገባው ነበር፣ ሆኖም የዕብራውያን መጽሐፍ በግልጽ እንደሚያስቀምጠው፣ ይህኛው ግን የሚሻል ኪዳን ነው ምክንያቱም አዲሱ ኪዳን የጸናው በአንድ ልጁ ደም ስለሆነና ኃጢአትን ሙሉ በሙሉ ሊያነጻ እንደማይችለው እንደ በሬዎችና እንደ ፍየሎች ደም ስላልሆነ ነው:: ስለዚህ፣ በአዲሱ ኪዳን ውስጥ መኖር፣ በረከቶቹን መቀበልና ምናልባትም በብሉይ ኪዳን ዘመን ሊይታወቁ የነበሩ ነገሮችን ማወቅ እጅግ አስደናቂ ነው::***

- ***ፓ/ር ዳግ ማክኮኔል***

ኤርምያስ ስለ አዲሱ ኪዳን የሰጠው መግለጫ እንደ ክርስቶስ ተከታዮች በእኔና በእናንተ ውስጥ ወሳኝ ጥያቄዎችን ሊጭር የሚችል መሆኑን ማየት አዳጋች አይሆንም:: የአዲስ ኪዳኑ ህዝብ በአገልግሎት ታማኝ እንዲሆን ጥሪ ማቅረብ የማያስፈልግ

ከሆነ፣ አዲስ ኪዳን ታዘዙ በሚሉ ጥሪዎች የተሞላው ታዲያ ለምንድን ነው? መርገም ስለሚያስከትሉ ነገሮች ማስጠንቀቅ አስፈላጊ ካልሆነ፣ ከክርስቶስ ፊታቸውን ለመመለስ የሚፈተኑ ሰዎችን አዲስ ኪዳን የሚያስጠነቅቀው ለምንድን ነው?

ለእነዚህ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት፣ በዚህ ትምህርት የዳሰስናቸውንና መጽሐፈ ኢያሱ በክርስቶስ ፍጻሜውን ስለሚያገኝባቸው መንገዶች የተመለከትናቸውን መለስ ብለን መቃኘት ይገባናል፡፡ እንደምታስታውሱት፣ እስራኤላውያንን በድል የመውረሰ ግቦች እና በሦስት ምዕራፎች ወይም እርከኖች የተከናወነውን የእስራኤልን የነገዶች የርስት ክፍፍል ክርስቶስ እንደሚፈጽማቸው አዲስ ኪዳን ያስተምራል፡፡ የመጀመሪያውን የእነዚህን ግቦች ፍጻሜ ማከናወን የጀመረው በመጀመሪያው መምጣቱ ወቅት መንግሥቱን ሲያበስር ነው፡፡ ቀጥሎም በቤተክርሰቲያን የታሪክ ዘመናት በመንግሥቱ መስፋፋት ወቅት መፈጸሙን ቀጠለ፡፡ ፍጻሜያቸውን ወደ ሙላት የሚያመጣውም ዳግመኛ በክብር በሚመጣበት በመንግሥቱ ፍጻሜ ወቅት ነው፡፡  ይህ የፍጻሜ ንድፍ እጅግ ወሳኝ ነው ምክንያቱም ኢያሱ በቃል ኪዳን ታማኝ እንዲሆኑ ያቀረበውን ጥሪ ኢየሱስም ወደ ፍጻሜ የሚያመጣቸው በእነዚህ ሦስት እርከኖች ስለሆነ ነው፡፡

የኢያሱን መጽሐፍ የመጨረሻ ክፍል ክርስቲያናዊ ተዛምዶ የምንመረምረው በተለመደው መንገድ ሲሆን በቃል ኪዳን ስለመታመን አዲሰ ኪዳን የሚያስተምረውን ንድፉን በመመልከት እንጀምራለን፡፡ አስቀድመንም በመንግሥቱ ብሥራት ወቅት በቃል ኪዳን መታመን እንዴት ፍጻሜውን እንዳገኘ እንመልከት፡፡

# ብሥራት

አዲሱ ኪዳን የጀመረው በክርስቶስ የመጀመሪያ መምጣት ወቅት እንደሆነ በእርግጠኝነት እናውቃለን፡፡ በሉቃስ 22፡20 ውስጥ፣ ኢየሱስ ራሱ “በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን” በማለት ተናግሯል፡፡ በዕብራውያን 8፡6 ውስጥ፣ ኢየሱስ የአዲሱ ኪዳን መካከለኛ እንደሆነ እናነብባለን፡፡ ደግሞም በ2ኛ ቆሮንቶስ 3፡6 ውስጥ፣ ሐዋርያው ጳውሎስ ስለራሱና ስለ ባልንጀሮቹ ሲናገር “የአዲስ ኪዳን አገልጋዮች”ነን በማለት ይናገራል፡፡

> ***በወንጌላት ውስጥ ማብራሪያ እንደተሰጠበትና በመጨረሻው ራት ላይ ጌታ ኢየሱስ እንዳመለከተው፣ የእርሱ መስዋዕታዊ ሞት በሁለት እርከኖች ወሳኝነት አለው፡፡  አዎን፣ ሞቱ ስለ እኛ ኃጢአት ሲል የቅዱሱ እግዚአብሔር ቁጣ በእርሱ ላይ ያረፈበት የማስተሰርያ መስዋዕት ሲሆን ከእርሱም የተነሳ እኛ ከፍርድ አምልጠናል፣ ሆኖም ደግሞ የእርሱ ሞት የቃል ኪዳን ማቆሚያ መስዋዕት ሆኗል፡፡ የእርሱ ደም አዲስ ኪዳንን መስርቷል፣ ያንንም በማቴዎስና በሉቃስ ውስጥ በግልጽ አስቀምጧል፡፡ ስለዚህ፣ የእርሱ ሞት የአዲሱን ኪዳን ዘመን የጀመረ መስዋዕት ሆኗል፡፡***
>
> \- ***ዶ/ር ቻርለስ ኤል. ኳርለስ***

ክርስተስ አዲሱን ኪዳን ያበሰረበትን መንገድ አዲስ ኪዳን በሁለት መንገድ አስምሮበታል፡፡ በአንድ መንገድ፣ የኢየሱስን ሥራ እንደ መሲህ አትኩሮት ሰጥቶ ዘግቦታል፡፡ ኢያሱ አስቀድሞ እንዳይመጣባቸው ሲያስጠነቅቅ እንደነበረው እስራኤል ለበርካታ መቶ ዓመታት በምርኮ እርግማን ስር ስትሰቃይ ከርማለች፡፡ አብም ከምንም ጋር ሊወዳደር በማይችል መንገድ በጎነቱንና ምህረቱን ኢየሱስን በመላክ አፈሰሰው፡፡ የስላሴ ሁለተኛ አካል የሆነው እርሱ ትልቁ የዳዊት ልጅ ሆኖ ፍጹም ሰው ሆኖ ለቃል ኪዳን ታምኝ ስለመሆን እግዚአብሔር ያስቀመጠውን መስፈረት በሙላት እና በፍጹምነት አሳካ፡፡ ያንንም ያደረገው በሞትና በእርሱ ለሚያምኑ ሁሉ የኃጢአትን ስርየትን በማስገኘት ነው፡፡ ከዚህ አገልግሎቱ የተነሳም፣ እግዚአብሔር በትንሣኤ በረከት ባረከው በሁሉም ላይ ገዢ ይሆን ዘንድ ወደ ሰማይ እንዲያርግ አደረገው፡፡ አዲስ ኪዳን በተጨማሪም የሚነግረን እውነተኛ አማኞች አሁን “በክርስቶስ” ናቸው፣ ያም ማለት በሰማይ መንበር ፊት በክርስቶስ ውስጥ ሆነው ማለት ነው፡፡ ከክርስቶስ ላይ በክብር ነግሠን በሰማያት ተቀምጠናል፡፡

በሌላ ጎኑ ግን፣ ኢየሱስ መንግሥቱን ባበሰረበት በመጀመሪው መምጣቱ ወቅት በተከናወኑት አስደናቂ ሥራዎች ኤርምያስ ስለ አዲሰ ኪዳን በትንቢቱ የተናገረው ነገር በቤተክርሰቲያን ውስጥ በሙላትና በፍጽምና አልተገለጠም፡፡ በመጀመሪያው ምዕተ-ዓመት ቤተክርስቲያን ውስጥ፣ ሐዋርያው ጳውሎስ በ2ኛ ቆሮንቶስ 11፡26 እና በገላትያ 2፡4 እንደሚጠራቸው “ሐሰተኛ ወንድሞች” ነበሩ፡፡ ንስሓ የማይገቡ ከሆነ፣ እነዚያ ሐሰተኛ ወንድሞች በእግዚአብሔር የዘላለም ፍርድ ስር መውደቃቸው አይቀሬ ነው፡፡ እውነተኛ አማኞች ግን፣ “በክርስቶስ” መሆን ብቻ ሳይሆን በዚህ ምድር በምንኖርበት ዘመን ሁሉ ክርስቶስ

በቅዱስ መንፈሱ አማካይነት እርሱ በእኛ ውስጥ ይኖራል፡፡ መንፈስ ቅዱስም እውነተኛ አማኞችን በህይወት ዘመናቸው ሁሉ በውስጣቸው በመሥራት በእውነተኛ ቅድስና ሂደት ውስጥ ይመራቸዋል፣ ያም በ2ኛ ቆሮንቶስ 7፡1 "በእግዚአብሔር ፍርሃት ቅድስናን ፍጹም እያደረግን" እንደተባለው ማለት ነው፡፡

ኢየሱስና የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች በተደጋጋሚ አፅንኦት ሰጥተው በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ከተከናወኑትና ኢያሱ በንግግሮቹ ማስጠንቀቂያ ከሰጠባቸው የቃል ኪዳን ገጽታዎች ጋር ተመሳሳይ በሆነ መንገድ ለምን እንደተከናወነ ምድራዊ እውነታዎች ያብራራሉ፡፡ ልክ ኢያሱ እስራኤልን ወደ ቃል ኪዳን ተሃድሶ እንደመራ ሁሉ፣ ኢየሱስና ሐዋርያቱም የአዲሰ ኪዳንን የቃል ኪዳን ተሃድሶ በሚያጸና መልክ ቃሉን በቋሚነት በመስበክና የጌታን ራት በዓላማ አከናውነዋል፡፡

ደግመው ደጋግመው፣ የእግዚአብሔርን በጎነት አስምረውበታል፡፡ ሆኖም ደግሞ ቤተክርስቲያን ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆና እንድትዘልቅም ጥሪያቸውን አቅርበዋል፡፡ በሁላችን ዘንድ በውል በሚታወቀው በሮሜ 12፡2 ውስጥ፣ "በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ።" በማለት አሳስበዋል፡፡ በጨማሪም ደግመው ደጋግመው ከክርስቶስ ዘወር ያሉት ሁሉ ስለሚጠብቃቸው የእግዚአብሔር ፍርድ በዘመናቸው የነበረችውን ቤተክርስቲያን አስጠንቅቀዋል፡፡ በዕብራውያን 10፡29 እንደምናነብበው፣ "የእግዚአብሔርን ልጅ የረገጠ ያንንም የተቀደሰበትን የኪዳኑን ደም እንደ ርኩስ ነገር የቆጠረ የጸጋውንም መንፈስ ያክፋፋ፥ እንዴት ይልቅ የሚብስ ቅጣት የሚገባው ይመስላችኋል?" ይላል፡፡ ልክ ኢያሱ በዘመኑ ስለ ቃል ኪዳን ብርቱ ማስጠንቀቂያ እንደሰጠ ሁሉ፣ ይህና ሌሎችም ተጨማሪ የአዲስ ኪዳን ምንባቦች እንደሚያሳዩን ሐሰተኛ ወንድሞች ለድነት ወደሚበቃው እምነት እንዲመጡ ያሳስባሉ፡፡ እውነተኛ ወንድሞች ለእግዚአብሔር በታማኝነት አገልግሎታቸውን በማቅረብ እንዲቀጥሉ ያሳስባሉ፡፡

በዚህ መረዳት መሠረት፣ በኢያሱ መጽሐፍ የመጨረሻ ምዕራፎች ውስጥ የተነሱት አምስቱ መሪ ሃሳቦች በአዲሱ ኪዳን ብሥራት ላይም እንደተፈጸሙ ማየት አዳጋች አይሆንም፡፡ በኢያሱ መጽሐፍ የመጨረሻ ክፍል ውስጥ የተገለጠውን መለኮታዊ ሥልጣን ስንመለከት፣ ክርስቶስ በመጀመሪያው መምጣቱ ወቅት መለኮታዊ ሥልጣንን በላቀ መንገድ አንደሚፈፅመው ተመልክተን ነበር፡፡ በኢያሱ መጽሐፍ የተዘገበውን የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ገጽታዎች ስንመለከትም፣ ክርስቶስ እንዴት አድርጎ የአዲሱን ቃል ኪዳን ገጽታዎች እንደሚያጸናቸው ተመልክተናል፡፡ ኢያሱ አጽንዖት የሰጠበት የሙሴ ህግ ስነ-ልክም ልባችንን ወደ ክርስቶስ ፍጹም መታዘዝና በእርሱ የሚያምኑትም በአዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር ህግ ስነ-ልክ መሠረት እንዲመላለሱ ከቀረበላቸው ጥሪ ጋር ይዛመዳል፡፡ ደግሞም ኢያሱ እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ የገለጠውን ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይል ስንመለከት እኛም በክርስቶስ መንግሥት ብሥራት ወቅት ለእግዚአብሔር ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይል እውቅና እንድንሰጥ ያነሳሳናል፡፡ በመጨረሻም፣ በኢያሱ መጽሐፍ የመጨረሻ ክፍል ውስጥ የቀረበው የመላው እስራኤል አንድነት ጉዳይ፣ የሚያሳስበን ኢየሱስና ሐዋርያቱ ቤተክርስቲያን አንድ እንድትሆን ያቀረቡትን ጥሪ ነው፡፡

ለቃል ኪዳን መታመን በክርስቶስ መንግሥት ብሥራት ወቅት የሚፈጸምበትን ክርስቲያናዊ ተዛምዶ በማስከተል፣ ኢያሱ ለቃል ኪዳን ተሃድሶ ያቀረበው ማስጠንቀቂያና ጥሪ በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የክርስቶስ መንግሥት በሚስፋፋበት ወቅት እንዴት እንደሚዛመድ እንመለከታለን፡፡

## መስፋፋት/ዕድገት

በመጀመሪው ክፍለ ዘመን የነበረውን የክርስቶስን መንግሥት በዚህ ዘመን ካለው ከእርሱ መንግሥት ጋር ስናነጻጽረው፣ በክብር ያረገው ክርስቶስ በርካታ ነገር እንደፈጸመ በግልጽ እናስተውላለን፡፡ ላለፉት ሁለት ሚሊኒየሞች፣ ሰማይንና ምድርን ሲገዛ፣ የእርሱ ቤተክርስቲያን ደግሞ በመላው ዓለም እጅግ ተስፋፍታለች፡፡ እስከ እኛም ዘመን ድረስ መስፋፋቱን ቀጥሏል፡፡

በክብር ያረገው ክርስቶስ በጠላቶቹ ላይ ድልን ቢቀዳጅም፣ በቃል ኪዳን ታማኝ ሆነው እንዲዘልቁ ኢያሱ ያቀረበው ጥሪ በእኛ ዘመን በምትኖረውም ቤተክርስቲያን ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

በአንድ ወገን፣ ክርስቶስ ራሱ አሁንም በሰማያት ነግሷል ደግሞም በሰማያዊው ዙፋን ህዝቡን ሁሉ መወከሉን ቀጥሏል፡፡ እኛ “በክርስቶስ ነን” በእርሱ በማመን ወደሚገኘው ለድነት የሚያበቃ እምነት ለሚመጡ ሁሉ እግዚአብሔር የክርስቶስ ጽድቅ ለእያንዳንዱ ሰው እንዲቆጠር አድርጓል በዚያም በእርሱ የተረጋገጡትን ሰማያዊ በረከቶች ይቀበላሉ፡፡ ከዚህም ባሻገር፣ ኃጢአትን በምናደርግበት ወቅት፣ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ፊት ስለ እኛ ይማልዳል፡፡ በዕብራውያን 7፡25 “ስለ እነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል።” ተብሎ እንደተጻፈው ማለት ነው፡፡

በሌላ በኩል ግን፣ በምድር የምትኖረው የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ከፍጽምና እጅግ ርቃ ግን ወደዚያው የምትገሰግስ ሆና ትዘልቃለች፡፡ እኛም አዘውትረን በዕብራውያን 12፡14 እንደተጻፈው፣ “ከሰው ሁሉ ጋር ሰላምን ተከታተሉ ትቀደሱም ዘንድ ፈልጉ፥ ያለ እርሱ ጌታን ሊያይ የሚችል የለምና።” አሁንም ቢሆን አማኞች ነን እያሉ “ሐሰተኛ የሆኑ ወንድሞች” አሉ፡፡ የነገረ-መለኮት ምሁራኑም “ግብዞች” ወይም “እምነታቸው በጊዜያዊ ነገር ላይ የተመሰረተ” ይሏቸዋል፡፡ እንዲያውም ክህደት በቤተክርስቲያን ውስጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ሄዷል፣ ስለዚህም በ1ኛ ቆሮንቶስ 10፡12 ውስጥ “ስለዚህ እንደ ቆመ የሚመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ።” ተብሎ የተሰጠውን ማስጠንቀቂያ የማወጅ ሙብት አለን፡፡

እርግጥ ነው፣ በእግዚአብሔር ምህረት ክርስቶስ በመንፈሱ የሚኖርባቸው ጥቂት እውነተኛ አማኝ የሆኑ ቅሬታዎች ይኖራሉ፡፡ ሆኖም ግን እግዚአብሔር በተለያዩ ጊዜያዊ መከራዎች ውስጥ በማሳለፍ እየቀጣ በሥነ-ሥርዓት ያሳድጋቸዋል፡፡ ኢየሱስ በራእይ 3፡19 ውስጥ የሎዶቅያን ቤተክርስቲያን፣ “እኔ የምወዳቸውን ሁሉ እገሥጻቸዋለሁ እቀጣቸውማለሁ፤ እንግዲህ ቅና ንስሐም ግባ።” በማለት እንደተናገራት ማለት ነው፡፡

> ***እግዚአብሔር ለህዝቡ ያለውን ፍቅር የሚያሳይበት መንገድ በዚህ ዓለም በሚኖሩበት ዘመን በሕይወታቸው የስነ-ሥርዓት ቅጣትን መላክ ነው፡፡ ስለዚህ፣ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሲሞት ዘላለማዊ ርግማናችንን መውሰዱ አስደናቂ ቢሆንም፣ በዚህ ምድር ሕይወታችን በምንኖርበት ኑሮም መከራዎችን ሁሉ፣ ፈተናዎችን ሁሉ፣ ቅጣቶችን ሁሉ አልፎም በቃል ኪዳኑ ላይ የተጠቀሰቱን እርግማናች ሁሉ ከእውነተኛ አማኞቹ ላይ አለመውሰዱም ሌላው የእግዚአብሔር አስደናቂ ስጦታ ነው፡፡ ምክንያቱም እነዚያ ሁሉ እኛን ወደ ቅድስና እና ወደ ጽድቅ የሚመራባቸው መሣሪያዎቹ ሲሆኑ ያም በሚመጣው ዓለም የምንቀበለውን የተትረፈረፈ ባርኮት በዕለት ከዕት እይወታችን ገሃድ ሆኖ የምናስተውልበት ነው፡፡***
>
> \- ***ዶ/ር ሪቻርድ ኤል. ፕራት. ዳግማዊ***

በኢያሱ መጽሐፍ የመጨረሻ ክፍል ውስጥ የተነሱት መሪ ሃሳቦች በክርስቶስ መንግሥት መስፋፋት ወቅት ለምትገኘው ቤተክርስቲያንም ብዙ የሚያስተላልፉት መልእክቶች እንዳሉ ግልጽ ነው፡፡ በኢያሱ መጽሐፍ በዚህኛው ክፍል ውስጥ የሚገኘው መለኮታዊ ሥልጣን በዛሬው የግል ሕይወታችንና በቤተክርስቲያን ውስጥ ክርስቶስ ባለሥልጣን እንደሆነ ያሳስበናል፡፡ በኢያሱ መጽሐፍ የተገለጸው የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ገጽታዎች በክርስቶስ የተገለጡትን የአዲስ ኪዳን ገጽታዎች ተግባራዊ ለማድረግ የሚቀሰቅሱን ሲሆን፣ ያም ሊሆን የሚችለው ለእግዚአብሔር በጎነት እውቅና ስንሰጥ፣ ለእርሱ ታማኝነታችንን ስንገልጽናየቃል ኪዳኑን ትሩፋት ስንቀበል ነው፡፡ የኢያሱ መጽሐፍ በሙሴ ህግ ስነ-ልክ ላይ የሰጠውን አጽንኦት ስናነብብ፣ ልንመለከተው የሚገባን ብሉይ ኪዳንን በክርስቶስ ፍጻሜውን ካገኘው አዲስ ኪዳን መነጽር ሲሆን ያንንም የምናደርገው የዕለት ከዕለት ሕይወታችን መመሪያ እንዲሆን በመፍቀድ ነው፡፡ እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ የገለጸውን ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይል ኢያሱ እንዳወሳው ሁሉ፣ በዚህም ዘመን እግዚአብሔር በኢየሱስ አማካይነት በቤተክርስቲያን ውስጥ በገለጠው ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይል ልንደሰት ይገባል፡፡ እናም፣ በእርግጥ፣ በኢያሱ መጽሐፍ ውስጥ የተወሳው የእስራኤል አንድነት ጉዳይም በክርስቶስ አማካይነት የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ህዝብ የሆንን ሁላችን ቤተክርስቲያን በመላው ዓለም ስትስፋፋ አንድነታችንን እንድንጠብቅ ጥሪውን ያቀርብልናል፡፡

እንደተመለከትነው፣ የኢያሱ መጽሐፍ የመጨረሻ ክፍል ክርስቲያናዊ ተዛምዶ የሚያተኩረው ክርስቶስ በመንግሥቱ ብሥራት ወቅት ምን እንዳከናወነና በእኛም ዘመን እንዴት እንደሚስፋፋ ነው፡፡ በዚህ ብቻ ሳይሆን ክርስቶስ ዳግመኛ ከሚመለስበትና እነዚህን ጉዳዮች ሁሉ ወደ ፍጽምና ከሚያመጣበትም ወቅትም ጋር ተዛማጅነት አላቸው፡፡

# ፍጻሜ

በአንድ ወገን፣ ክርስቶስ ዳግመኛ በክብር ሲመለስ እርሱ ራሱ በአዲሲቷ ሰማይና ምድር በቃል ኪዳኑ ታማኝ ስለመሆኑ ብድራት ይሆን ዘንድ ሁሉን በሙላት ይወርሳል፡፡ በራዕይ 11፡15 ውስጥም፣ በዚያን ወቅት፣ "የዓለም መንግሥት ለጌታችንና ለእርሱ ለክርስቶስ ሆነች፥ ለዘላለምም እስከ ዘላለም ይነግሣል" ተብሎ ተጽፎ እናነብባለን፡፡ በፊልጵስዩስ 2፡11 ደግሞ፣ "መላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደ ሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው።" የሚሉ ቃላት እናነብባለን፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ፣ ክርስቶስ ዳግመኛ ሲመጣ፣ ቤተክርስቲያንና ዓለም ሁሉ ፍጹም ይነጻሉ ደግሞም ይከብራሉ፡፡ በዚህ ዘመን የማያምኑ ሁሉ ከእግዚአብሔር የሚቀበሉት የፍጥረት ጸጋ ዘላለማዊ ፍርዳቸው አይቀሬ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በዚህ ዘመን የሚደርስባቸው እርግማን ወደፊት ለዘላለም የሚብቃቸው ፍርድ ማሳሰቢያ ነው፡፡ በክርስቶስ የሚያድነውን እምነት የተቀበሉ ሁሉ ግን በአዲሱ ፍጥረት ከእርሱ ጋር ባርኮቱን ተካፋይ ይሆናሉ፡፡ በዚህ ዘመን የሚቀበሉት የትኛውም በረከት ወደ ፊት የእነርሱ የሚሆኑት የዘላለም ክብሮች ቅምሻዎች ናቸው፡፡ ደግሞም በዚህ ዘመን ለጊዜው የሚያልፉባቸው ቅጣቶችም ወደፊት የዘላለም ብድራትን የሚያስገኙላቸው ናቸው፡፡ ያዕቆብ በ1፡12 እንዳስቀመጠው፡ "በፈተና የሚጸና ሰው የተባረከ ነው፤ ከተፈተነ በኋላ ለሚወዱት ተስፋ ስለ እርሱ የሰጣቸውን የሕይወትን አክሊል ይቀበላልና።" በዚያን ቀን፣ የአዲሱ ኪዳን ተስፋዎች በመላት ይፈጸማሉ፡፡ በራእይ 22፡3 እንዲህ እናነብባለን፡ "ከእንግዲህም ወዲህ መርገም ከቶ አይሆንም። የእግዚአብሔርና የበጉም ዙፋን በእርስዋ ውስጥ ይሆናል፥ ባሪያዎቹም ያመልኩታል፥ ፊቱንም ያያሉ፥"

የኢያሱ መጽሐፍ የመጨረሻ ክፍል መሪ ሃሳቦች በክርስቶስ መንግሥት ፍጻሜ ወቅት የሚጠብቀንን ትልቅ ተስፋ በግልጽ ያሳየናል፡፡ በኢያሱ መጽሐፍ በዚህኛው ክፍል የተገለጠው መለኮታዊ ሥልጣን በክርስቶስ በኩል የተቀበልነው ተስፋ በእግዚአብሔር ሙሉ ሥልጣን የጸና እንደሆነ ያሳስበናል፡፡ ኢያሱ በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ላይ የሰጠው ትኩረት አንድ ቀን እኛም ከክርስቶስ ፍጹም መታመን የተነሳ ብድራትን እንደምንካፈል በማሰብ እንድንደሰት ያነሳሳናል፡፡ በኢያሱ አጽንዖት የተሰጠው የሙሴ ህግ ስነ-ልክ ወደ ፍጽምና የሚመጣው እኛ ከክርስቶስ ጋር በአዲስ ፍጥረትነት ስንዋሃድ በምናሳየው ፍጹም የሆነ የእግዚአብሔር ፈቃድ መታዘዝ እንደሆነ በማሳሰብ ያበረታታናል፡፡ እግዚአብሔር ለእስራኤል ስለ ገለጠው ልዕለ-መለኮታዊ ኃይል ኢያሱ የሰጠው ትኩረት ክርስቶስ ዳግመኛ ሲመለስ ስለሚገለጠው ወደር የለሽ ኃይል እንድናሰላስል ይቀሰቅሰናል፡፡ በመጨረሻም፣ በኢያሱ መጽሐፍ በዚህኛው ክፍል ላይ አጽንኦት የተደረገበት የእስራኤል አንድነት በክርስቶስ መንግሥት ፍጻሜ ወቅት፣ አዲሲቷ ዓለም እርሱን በሚያመልኩና በማያልቅ ሃሴት በሚያገለግሉት በእግዚአብሔር ታማኝ ህዝብ የምትሞላ መሆኗን በማሰብ እንድንቦርቅ ያደርገናል፡፡

# ማጠቃለያ

በእስራኤል የቃል ኪዳን መታመን ላይ ባተኮረው በዚህ ትምህርት፣ የኢያሱን መጽሐፍ የመጨረሻ ዋና ክፍል መርምረናል፡፡ ኢያሱ ለቀደምት ተደራሲኑ በሰጠው የቃል ኪዳን ማስጠንቀቂያ ተደራሲያኑ የታመነ አገልግሎት እንዲያቀርቡ ጥሪ ሲያቀርብላቸው ባለመታመናቸው ስለሚጠብቃቸው ፍርድ ማስጠንቀቁን አይተናል፡፡ እስራኤል ቃል ኪዳኗን የማደሷ ነገር ቀደምት ተደራሲኑም በእነርሱ ዘመን ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ቃል ኪዳን እንዲያድሱ እንዴት መንገዱን እንዳመለከታቸው አይተናል፡፡ የኢያሱ መጽሐፍ የዚህኛው ክፍል ክርስቲያናዊ ተዛምዶው መሠረቱን ያጠበቀው የእስራኤል ለቃል ኪዳን መታመን በክርስቶስ መንግሥት ብሥራት፣ መስፋፋት እና ፍጻሜ ወቅት እንዴት በክርስቶስ ወደ ግቡ እንደደረሰ ተመልክተናል፡፡

የኢያሱ መጽሐፍ የመጨረሻ ክፍል አጠቃላይ መጽሐፉ ለቀደምት ተደራሲያኑ ያለውን ፋይዳ በገሃድ ያሳየ ነው፡፡ እግዚአብሔር ህዝቡን በድል አድራጊነት እንዲወርስ ደግሞም እያንዳንዱ የእስራኤል ነገድ የየራሱን ርስት እንዲከፋፈል በማድረግ ባርኳል፡፡ እነዚህ የመለኮታዊ በጎነት መገለጫዎች የመጽሐፉን ቀደምት ተደራሲያን ለቃል ኪዳናቸው ታማኝ

ሆነው እንዲዘልቁ አድርገዋቸዋል፡፡ ለእርሱ በእምነትና በአገልግሎት ምላሽ መስጠት በተሳናቸው ላይ ደግሞ የእግዚአብሔር ብርቱ ፍርድ ትወድቅባቸዋለች፡፡ ለእግዚአብሔር ምህረት በትሁት መሰጠት ምላሽ የሚሰጡ ሁሉ ግን ታላቅ ብድራት ይጠብቃቸዋል፡፡ ለእኔና ለእናንተም እንዲሁ ነው፡፡ በክርስቶስ፣ ታላቁን የእግዚአብሔር ጸጋ ተቀብለናል፡፡ በአዲሲቷ ምድርና ሰማይም በክርስቶስ አማካይነት እግዚአብሔር ዘላለማዊ ድልንና ዘላለማዊ ርስትን ይሰጠናል፡፡ እነዚህ በረከቶች የሚፈጸሙት ደግሞ በሚያድን እምነት ወደ ክርስቶስ ለሚመጣ ሁሉ ነው፡፡